# የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲና ችግሮቹ

**በገብሩ አሥራት/ዓረና/**

1. **መግቢያ**

አውሮጳ ውስጥ «መካከለኛ ዘመን» ተብሎ በሚታወቀው እ.ኤ.አ ከ1000 ዓ.ም እስከ 1453 ዓ.ም የዘለቀው ዘመን የመሣፍንት አገዛዝ ሥር የሰደደበት ሁኔታ ነበር። ይህን ዘመን ተከትሎ የተከሰተው መጠነኛ የንግድ፣ የዕደ ጥበብና የባህል ዕድገት ከመሬት ውጭ ሀብት በግለሰቦች እጅ እንዲከማች አስቻለ። እነዚህ ከፍተኛ ሀብት ያከማቹት ቡርጊሶች በጊዜው በነበሩት የፖለቲካ ሥርዓቶች ተገቢው ቦታ ይኖራቸው ዘንድም ተፅእኖዎችን ማሳደር ጀመሩ። ይኸውም በነበረው የነገሥታቱ ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ ፖለቲካዊ ሥልጣን የማሻሻያ ለውጥ ተደርጎ የተወሰነ ሥልጣን እንዲጋሩ ጥያቄዎችን ያቀርቡ ጀመር። ይህ የቡርጊሶች የለውጥ እንቅስቃሴ እያየለ በመሄዱ በአንዳንድ አገሮች የተወሰነ ስልጣን የማጋራት ለውጥን አስከተለ።

የኢንዱስትሪው አብዮትና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ተከትሎ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የተከሰተው ከፍተኛ የግል ሀብት ክምችት እምርታ ደግሞ ፍፁም የዘውድ አገዛዝ ጊዜው ያለፈበትና የዕድገት እንቅፋት አድርጎ ተመለከተው። በመሆኑም በተደረጉት የሥልጣን ጥያቄ እንቅስቃሴዎች የተነሣ በአንዳንድ አገሮች የኃይል ሚዛኑን በሚለውጥና ለከበርቴዎች በሚያዳላ አኳኋን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግሽግ ተደረገ። በተወሰኑ አገሮች ደግሞ ይህን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግሽግ ባለመቀበላቸው «የከበርቴው አብዮት» ተብሎ የሚታወቀው ነውጠኛ የሥልጣን ሹም ሽርን አስከተለ። ከነዚህ የታወቁት የከበርቴው አብዮቶች መካከል እ.ኤ.አ በ1879 ዓ.ም በፈረንሳይ የተካሄደው ተጠቃሽ ነው። የዚህ የከበርቴው አብዮት መሪ መፈክር «ነጻነት፣ እኩልነትና ወንድማማችነት» የሚል ሲሆን በዋነኛነት ያጠነጠነው በግል ሃብት ቅዱስነትና የግለሰብ ነጻነት ዙሪያ ነበር። ይኸም ለከበርቴው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ዕድገት መሠረት የሚጥል ነበር።

የከበርቴው ሥርዓት የበላይነትን ተቀዳጅቶ የተወሰነ ዘመን ካስቆጠረ በኋላ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አዳዲስ ፍልስፍናዎች፣ ርእዮተ ዓለሞችና ፖለቲካዊ ንድፈ ሐሳቦች ማቆጥቆጥ ጀመሩ። ከነዚህ መካከልም የግል ሃብት ቅዱስነትን

የማይቀበለውና የሰው ልጆች በተለይ ደግሞ ጭቁኖች ነጻ የሚወጡት የግል ሃብት ጠ ፍቶ የጋራ ሃብት ሲዳብር ነው የሚለው በነ ካርል ማርክስ የሚራመድ አስተሳሰብ ነበር። ስለሆነም ከበርቴውን የግል ሀብት ባለቤትነትንና የፖለቲካ ሥልጣን ቁጥጥርን የሚያሳጣው የላብ አደር ወይም የሶሻሊስት አብዮት መካሄድ እንዳለበት ታወጀ። በዚህ አዋጅና መፈክር መሠረትም ላብ አደሮች ተደራጅተው ሥልጣን የመቆጣጠር ሙከራዎችን አደረጉ።

በኢንዱስትሪ ባደጉትና በበለፀጉት የምዕራብ አውሮፓ አገሮች የተካሄዱት የሶሻሊስት አብዮቶች ድል ሳይቀዳጁ ዓመታትን ካስቆጠሩ በኋላ በተነጻጻሪ ዝቅተኛ ዕድገት በነበራትና አብዛኛው ሕዝቧ አርሶ አደር በሆነው ሩስያ አዲስ አስተሳሰብ ብቅ አለ። ይኸውም አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል አርሶ አደር በሆነበት አገር መካሄድ ስላለበት አብዮት በቪላድሚር ኢሊች ሌኒን የተቀነቀነው ንድፈ ሐሳብ ነበር። በዚሁ በሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብ መሠረት አብዛኛው ሕዝባቸው አርሶ አደር በሆኑባቸው አገሮች ሁለት ተከታታይ አብዮቶች መካሄድ እንዳለበት ይተነትናል። የመጀመሪያው አብዮት «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ሲሆን እሱን ተከትሎ የሚካሄደው ደግሞ «ሶሻሊስት አብዮት» ይለዋል። በዚህ መሠረት እ.ኤ.አ የካቲት 1917 ዓ.ም በሩስያ የተካሄደውን አብዮት «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ሲለው ከስድስት ወራት በኋላ እ.ኤ.አ ጥቅምት 21 ቀን 1917 ዓ.ም የተካሄደው አብዮት ደግሞ የሶሻሊስት አብዮት ይለዋል። እንግዲህ አብዮታዊ ዲሞክራሲያ የሚባለውና ቀደም ሲል በአውሮጳ ከተካሄደው የከበርቴው አብዮት በመሠረቱ ይለያል የተባለው አብዮት ለመጀመሪያ ጊዜ ሥያሜውን ያገኘው በሌኒን አማካይነት ሶቭየት ኅብረት ውስጥ መሆኑ ነው። ከዚህ በኋላም በርካታ ያልበለጸጉና በቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩ አገሮች የሚያካሂዱት አብዮት «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚል ሥያሜ ሰጥተውታል። በአገራችን የነበሩት የግራ ፖለቲካ ድርጅቶችም የሚያደርጉትን እንቅስቀሴ በዚሁ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ይጠሩት ነበር።

## 2. <u>የዓይነተኛ (ችለቷሰሰፀቾቷለ ? አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋነኛ ይዘቶች</u>

እ.ኤ.አ. በ1917 ዓ.ም በሌኒን የሚመራው አብዮታዊ ዴሞክራሲና የሶሻሊስት አብዮት ተካሄዶ ድል ከተቀዳጀ በኋላ የቀድሞዋ ሩስያ ሶቭየት ኅብረት የሚል አዲስ መጠሪያ ተሰጥቷት የመጀመሪያዋ ሶሻሊስት አገር ሆነች። ከዚህ በኋላ ሶቭየት ኅብረት የተለያዩ አገሮች አብዮታውያን መናኸሪያ በመሆን ዓለም ዓቀፍ እንቅስቃሴ

የሚቀጣጠልባት ማዕከል እንድትሆን ዕቅድ ተነደፈ። በርካታ ኮሚኒስቶችም ጉዟቸውን ወደ ሞስኮ በማድረግ እዚያ የተገኘውን ልምድ በመቀመር ለመሥራት ወሰኑ። በተለይ በ1919 ዓ.ም ከመላ ዓለም የተውጣጡ ኮሚኒስቶችን ያሰባሰበ ኮሚኒስት ኢንተርናሽናል /ችጸመፀነተጵረነ/ የሚል ድርጅት ተቋቋመ። ይህ ድርጅት በመላው ዓለም በሚገኙ ጨቋኝ ገዢ መደቦች ላይ አብዮት የሚቀጣጠልበትን ስልትና ስትራተጂ ቀየሰ።

ኮሚንተርን የኢምፔራሊዝም ደካማ ቋጠሮ ባላቸው ባልበለፀጉ አገሮች ስለሚካሄደው አብዮት የሩስያን ልምድ መሠረት በማድረግ እንደሚንቀሳቀስ አስታወቀ። በተለይ ባልበለፀጉትና ከፊል ቅኝ ግዛትና ቅኝ ግዛት በሆኑት አገሮች መካሄድ ያለበት አብዮት «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» መሆኑን አሰመሩበት። እንደ እነ ቻይና፣ ሕንድ፣ መካከለኛ ምስራቅ ወዘተ. የመሳሰሉ አገሮች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተመርተው ወደ ሶሻሊዝም ሊገሰግሱ እንደሚችሉ ተነገረ። በመሆኑም በነዚህ አገሮች የሚገኙ ኮሚኒስቶችና አብዮተኞች የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዘትና ቁምነገር እንዲገነዘቡና በዛ ተመርተው እንቅስቃሴችን እንዲያቀጣጥሉ ጥሪ ቀረበ።

## 2.1 <u>የዓይነተኛ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ ይዘቶች</u>

አብዮታዊ ዴሞክራሲ አብዛኛው ሕዝባቸው አርሶ አደር በሆኑ አገሮች የሚካሄድ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ይዘት ያለው አብዮት ነው። በዚህ ፅንሰ ሐሳብ መሠረት ኢምፔሪያሊስቶችና ፊውዳሎች በጠላትነት ተፈርጀው ሥልጣናቸው በኃይልና በአብዮታዊ እርምጃ ይነጠቃሉ። ባልበለፀጉ አገሮች ዴሞክራሲ ሰፊ መሠረት እንዳይኖረውና ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት እንዳይሆን ማነቆ የሆኑት እነዚህ ሁለት ጣምራ ኃይሎች ወይም ጠላቶች ናቸው ከሚል ስሌት በመነሣት በነዚህ ኃይሎች ላይ ዓመጽ በማስነሣት ሥልጣናቸው መንጠቅ ሕጋዊም ፍትሐዊም ነው ስለሚባል በአብዮት እንዲመቱ ይደረጋል። በቅኝ ገዥዎች የሚሰቃዩት ሕዝቦችም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ አብዮት በማቀጣጠል ነጻነታቸው እንዲቀዳጁና አርነት እንዲጐናፀፉ ይመከራል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ በኢምፔሪያሊስቶችና በፊውዳሎች ላይ የሚያቀጣጥለው አብዮት በላብ አደሩ ፓርቲ መሪነትና በላብ አደሩና በአርሶ አደሩ መደቦች አጋርነት እንደሚካሄድም ይገልጻል። በዚህ መሠረትም ላብ አደሩ የአብዮቱ ግምባር ቀደም መሪ ሲሆን አርሰ አደሩ ደግሞ የአብዮቱ አጋርና የጀርባ አጥንት ተደርጎ ይወሰዳል። ከነዚህ ውጭ ያሉት ማኅበራዊ ኃይሎችም የተለያየ ሚና እንደሚኖራቸው በስትራተጂው ውስጥ ታሳቢ ይደረጋል። በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስተራተጂ እጅግ ደካማ የሆነው አገራዊ

ከበርቴ /ቡርዣ/ በተወላዋይነት ይፈረጃል:: የሚያወላውሉም በጠላትነት በተፈረጁት ኢምፔሪያሊስቶችና ፊውዳሎች መካከልና በአብዮቱ ዋነኛ ኃይሎች ማለትም በላብ አደሩና በአርሶ አደሩ መካከል ነው ይለዋል:: ከዚህ ውጭ ያሉትን ንኡስ ከበርቴዎች የአብዮቱ አጋሮች አድርጎ ይመለከታቸዋል::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ መደቦችንና ማኀበራዊ ኃይሎችን ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎችንም እንዲሁ በጠላትነት፣ በወዳጅነትና በመኻል ሰፋሪነት ይፈርጃል:: በፅንሰ ሐሳቡ መሰረት ፓርቲዎች የተለያዩ መደቦችና ማኀበራዊ ኃይሎች ጥቅምን የሚወክሉ ተቋማት ናቸው:: በመሆኑም እያንዳንዱ ፓርቲ መታየት ያለበት ከቆመለት መደብ ወይም ማኀበራዊ ኃይል አንፃር ነው ይላል:: የወዛደሩን ፓርቲ በመወከል የቆመ ፓርቲ በአብዮቱ መሪነትና ወዳጅነት ይፈረጃል:: ገበሬውን የሚወክል ፓርቲ ካለም እንዲሁ በወዳጅነት ይፈረጃል:: ከዚህ በተፃራሪ ከኢምፔሪያሊስቶችና ፊውዳሎች ጋር የተቆራኙና የነዚህን ጥቅም ያራምዳሉ የሚባሉ ፓርቲዎች ደግሞ በጠላትነት ይፈረጃሉ:: በነዚህ በሁለቱ ዋነኛ ፓርቲዎች መሃል ይዋዥቃሉ የሚባሉትና የከበርቴውን ወይም የላይኛውን ንኡስ ከበርቴ የሚወክሉ ፓርቲዎች ደግሞ በወላዋይነት ተፈርጀው እንደየ ሁኔታው በጠላትነት ወይም በጊዜያዊ ወዳጅነት ይደለደላሉ::

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሌላው ይዘት የሚመሠረተው መንግሥት የላብ አደሩና የአርሶ አደሩ አምባገነንነት የሚያረጋግጥ መሆኑ ነው:: በላብ አደሩ ርእዮተ ዓለም መሠረት እስከ አሁን የነበረው ዴሞክራሲ የጥቂት ጨቋኝ ገዢ መደቦች ዴሞክራሲ ነው:: ሰፊው ህዝብ ዴሞክራሲ ተነፍጎ ቆይቷል:: በመሆኑም ጨቋኞች የነበሩት መደቦች መልሰው መጨቆን አለባቸው ይላል:: ከዚህ በመነሣትም ዴሞክራሲ ወገናዊ በመሆኑ ለጭቁኖች እንጂ ለጨቋኞች የሚነፈግ ይሆናል:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይላብ አደሩና የአርሶ አደሩ አምባገነንነት ነው ሲልም ዴሞክራሲን ለነዚህ መደቦች አጎናጽፎ ለጨቋኞች ግን ስለሚነፍግ ነው::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተለያዩ መንግሥታዊ አካላት ያላቸውን ተነጻጻሪ ነጻነትም -ቷጭተጸነጸመየ? አይቀበልም:: የመንግሥታዊ አካላት አንዱ ሌላውን የመቆጣጠር ፅንሰ ሃሳብ የከበርቴው አስመሳይነት -ሀየፐጸቸረቷቸየ? ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም የለውም ይላል:: ሁሉም የመንግሥት አካላት ለአንድ ርእዮተ ዓለምና ለአንድ የመደብ ጥቅም እንዲያገለግሉ የተቋቋሙ ስለሆኑ የሥራ ክፍፍል እንጂ ሌላ ጥቅም አይኖራቸውም ይላል:: እነዚህ የመንግሥት ተቋማት የገዢው መደብ መጨቆኛ መሣሪያዎች ከመሆን ያለፈ ፋይዳ እንደማይኖራቸው ይገልጻል::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ቡርዣው ሊበራል ዴሞክራሲ ሲቪል ማኅበረሰቦች በመንግሥትና በኅብረተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሳመር ረገድ ሚና ይኖራቸዋል ብሎ አያምንም፡፡ በቡርዣው ሊበራል ዴሞክራሲ ሲቪል ማኅበረሰባት በኅብረተሰቡና በመንግሥት መካከል ያለውን የመራራቅ ክፍተት በሞምላት ረገድ የሚጫወቱት ሚና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመንበታል፡፡ ግዙፍ የመንግሥት መዋቅሮች በዜጎች /በኅብረተሰቡ/ ላይ ከባድ ተፅእኖ እንዳያሳድሩ በመመከት ረገድ ድርሻ እንዳላቸው ያምናል፡፡ በመሆኑም በነጻነት ተደራጅተው ሚናቸውን እንዲጫወቱ መፍቀድ ብቻ ሳይሆን እንዲጠናከሩም ያበረታታል፡፡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እይታ ግን እነዚህ ማኅበራት የቡርዣው መደብ አንድ ክፍል እንጂ ሌላ ሊሆኑ እንደማይችሉ ይታመናል፡፡ ከዚህ የተነሳም በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እምነት የሚቋቋሙት ማኅበራት በመሪ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ አብዮታዊው ፓርቲ የማይቆጣጠረው ማኅበር ከቶ ሊኖር አይችልም፣አይገባም፡፡ የማኅበራት ሚና የመንግሥትን ተጽእኖ መቋቋም መሆኑ ቀርቶ ኅብረተሰቡን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ይሆናሉ፡፡

በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የሚድያ ሚናም መንግሥትን ለማገልገል የተቋቋሙ ተቋም እንጂ ኅብረተሰብ የሚፈለገው እውነተኛ መረጃ እንዲያገኝ ለማድረግ የተቋቋመ ተደርጎ አይወሰድም፡፡ ነጻ ፕሬስ የሚባል ጉዳይም ቦታ አይኖረውም፡፡ «ለጭቁኖች ጥብቅና ከቆመውና» እነሱን ከሚያገለግለው መንግሥትና ፓርቲ ውጭ የሆነ ነጻ ፕሬስ ፈጽሞ ሊታሰብ አይችልም፡፡ ነጻ ፕሬስም ቢሆን የቡርዣው የማስመሰል ስልት እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር ነው፡፡ በመሆኑም በቡርዣው ሥርዓት ዴሞክራሲን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው የሚነገርለት ፕሬስም ነጻነት እንዲኖረው ተደርጎ አይደራጅም፡፡

የቡርዣው ዴሞክራሲ የዕድገት መሠረት ውድድር ነው ብሎ ያምናል፡፡ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የዕውቀት ዕድገት ምንጭ ውድድር ነው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ሥልጣንም ፓርቲዎች በሚያደርጉት ውድድር ይወሰናል ይላል፡፡ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እውን የሆነውም በዚህ የከበርቴው ሥልጣን በፖለቲካው ገበያ መወሰን አለበት የሚል አስተሳሰብ ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ አስተሳሰቡ የተለያዩ ጥቅሞችንና ማኅበረሰቦችን የሚወክሉ ፓርቲዎች ተወዳድረው በማሸነፍ ሥልጣን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል በሚለው መርህ ላይ ይመሠረታል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግን ይህንንም በአስመሳይነት

ይፈርጀዋል:: ከወዝ አደሩ ውጭ ያሉ ፓርቲዎች በመልክ የተለያዩ ቢመስሉም ዞሮ ዞሮ የሚወክሉት ግን አንድ መደብን ወይንም ቡርዥዋውን ነው ብሎ ያምናል:: ስለሆነም የብዙኃን ፓርቲን በመሠረቱ ይጻረራል:: በእርግጥ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚፈጠረው የአንድ ፓርቲ ሥርዓት ላይ የሚያሳድሩት የረባ ተጽኖ አይኖርም የሚል ግምገማ ላይ እስከደረሰና እስካመነ ድረስ የብዙ ፓርቲዎች ህልውና ሊፈቅድ ይችላል:: ይህ ግን የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ወይም ጠቅላይነትን መሠረታዊ አስተሳሰብ የሚለውጥ አይሆንም::

በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ «መሪ ድርጅት» -ቨቿነገጭቿረደ ፐቿረተየ? ልዩ ቦታ የሚሰጠው ነው:: የኅብረተሰብን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚመራና የሚቆጣጠር አንድ ጠንካራ ፓርቲ መኖር እንዳለበት የሚያምነው ይህ አስተሳሰብ ይህን ግዳጅ ለላብ አደር ወይንም ለኮሚኒስት ፓርቲው ይሰጠዋል:: በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ መሪ ድርጅት የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ ወዘተ. እንቅስቃሴዎችን በመምራትና በመቆጣጠር ወደ ፊት እንዲራመድ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል:: መሪ ድርጅት ዋነኛ የኅብረተሰብ እንቅስቃሴዎችን ብቻ ሳይሆን አነስተኛ የሚባሉትን እንቅስቃሴዎች ጭምር ይመራል፣ ይቆጣጠራል::

መሪ ድርጅት አባላቱን በተለያዩ መስኮች በማሰማራት ፖለቲካዊ አመለካከቱን ለማስረጽ ከመጣሩ በተጨማሪ ከላይ የሚወሰኑትን ውሳኔዎች ተግባራዊነትን ይቆጣጠ ራል:: መሪ ድርጅት ከማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም በላይ ሥልጣንና ኃይል ይኖረዋል:: ከዚህ የተነሣም የፓርቲ ሥልጣን ፍጹም ይሆናል:: በመሪ ድርጅት አሠራር መሠረት ከፓርቲው ውስጥም ማእከላዊ ኮሚቴውና ፖሊት ቢሮው ፍፁም ስልጣን ይኖራቸዋል:: በመሪ ድርጅት ፅንሰ ሐሳብ መሠረት የፓርቲው ፖሊት ቢሮን የሚስተካከል የሥልጣን ተቋም ከቶ አይኖርም:: በዚህ የፓርቲ የአመራር አካል የተወሰኑ ውሳኔዎች ያለምንም ማመንታት ተግባራዊ ይሆናሉ:: የፓርቲው ተራ አባላት በዴሞክራሲያዊ ማእከልነት ተሸብበው ከላይ የሚንቆረቆረውን ለመተግበር ይገደዳሉ:: ከላይ የሚወርደውን መመሪያ አልቀበልም ብሎ በፓርቲው ውስጥ ሊኖር የሚችል አባል ከቶ ሊኖር አይችልም::

ከሞላ ጎደል የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ ይዘቶች ከላይ የተጠቀሱት ሆነው የላብ አደሩና የአርሶ አደሩ አምባገነንነትን ወይም የበላይነትን ለማረጋገጥ የተቀየሱ ናቸው:: የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካ ላብ አደሩን ለሥልጣን ለማብቃት የሚወሰዱ

እርምጃዎችም ናቸው። በመሆኑም በአጭር ጊዜና በነውጥ ተግበራዊ እንዲሆኑ ይሞከራል።

2.2 <u>የዓይነተኛ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ ይዘት</u>

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባልበለፀጉ አገሮች የሚካሄድ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ትግል መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል። ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል አብዮት ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎችም አሉት። እነሱም ኢምፔሪያሊስቶችንና ፊውዳሎችን በማዳከም አርሶ አደሩንና ላብ አደሩን ያጠናክራሉ ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው።

ኢምፔሪያሊስቶችን በማዳከም ረገድ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የሚያዛቸው ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች ሁሉንም የኢምፔሪያሊስቶች ተቋሞች መውረስን ነው። የኢምፔሪያሊስቶች ኃይል የሚጠናከረው ካላቸው ኢኮኖሚያዊ ይዞታ የሚመነጭ ነው ብሎ ስለሚያምን ያለምንም ማወላወል ይዞታቸው እንዲወረስ ያደርጋል። ይህ እርምጃ ጉልበቱ የሚበዘበዘውና ሀብቱ የሚዘረፈው ሰፊው ሕዝብ ይዞታ እንደሚያጠናክር ታሳቢ ከማድረጉ ባሻገር አገራዊ ከበርቴው በቂ ቦታ ኖሮት ኢኮኖሚያዊ ዓቅሙ እንዲያሳድግ ያስችለዋል ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም የኢምፔሪያሊስቶች ሀብት መወረስ በመጀመሪያው ከሚወሰዱት የኢኮኖሚ እርምጃዎች አንዱ ይሆናል። የኢምፔሪያሊስቶች የኢንዱስትሪ ተቋማት መውረስ ጠንካራ አገራዊ ኢንዱስትሪ በመገንባት ረገድ አንድ ወሳኝ እርምጃ እንደሆነ የሚያምነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በተጨማሪም ወሳኝ ወይም ገዢ የሆኑትን የአገር የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋል እንዳለባቸው ያስረግጣል። በተለይ ገዢ የሆኑ የኢንዱስትሪ ተቋማትን ተቆጣጥሮ በአገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ተጽእኖ የማሳደር አቅጣጫ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነው። እነዚህ እርምጃዎች ቀጥሎ ለሚቋቋመው የሶሻሊስት ሥርዓት መሠረት ያመቻቻሉ ተብሎም ይታሰባል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከኢምፔሪያልስቶች ሀብት በተጨማሪ በፊውዳሎች ይዞታ ሥር ያለውን መሬትም ይወረሳል። በፊውዳሎች ብቻ ሳይሆን በአርሶ አደሮች ይዞታ ያለው መሬትም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይሆናል። መሬት በአጠቃላይ በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ሆኖ አርሶ አደሮች ተከፋፍለው የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል። ይህ እርምጃም ፊዳሎችን በማዳከምና የአብዮት ኃይሎችን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው አንድ ስትራቴጂያዊ ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫ ተደርጎ

ይወሰዳል፡፡ መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋሉና ለገበሬው መከፋፈሉ አብዛኛውን ሕዝብ በመንግሥትና በገዢው ፓርቲ ተጽእኖ ሥር በማዋል ለቀጣዩ ስትራቴጂያዊ እርምጃ ማለትም ለሶሻሊስት አብዮትና ግምባታ ዝግጁ እንዲሆን ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከፍ ብለው የተጠቀሱት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ አቅጣጫዎችና ይዘቶች ከፖለቲካዊ ይዘቱ ተለይተው የሚታዩ አይደሉም፡፡ የፖለቲካው ስትራተጂ አካል ሆነው ኢምፐሪያሊስቶችንና ፊዳሎችን በማዳከም ለሶሻሊስት አብዮትና ግምባታ መሠረት እንዲጥሉ የተቀየሱ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ፋይዳ ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

3. <u>የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲና ዕድገቱ</u>

ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተ ዓለምን የወረሰው ቀደም ብለው ከተቋቋሙት የግራና ግራ ዘመም እንቅስቃሴዎች ነው፡፡ የአፄ ኃይለ ሥለሴ መንግሥት ከመውደቁ በፊት ዓለማዊና አገራዊ ሁኔታዎች ለግራ እንቅስቃሴዎች መፈጠር የተመቻቹ ነበሩ፡፡ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በነሆ ቺ ሚንሀ የሚመራው የቤትናም ጦርነት፣ በነቸ ቼ ጉቬራና ፊደል ካስትሮ የሚመራው የኩዩባ አብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ የሶቭየት ኅብረት የወቅቱ አስገራሚ ዕድገት፣ የቻይና እንቅስቃሴና በአፍሪቃ ይካሄዱ የነበሩት የነጻነት እንቅስቃሴዎች በተለይ ደግሞ የሞዛምቢክና የአንጎላ ግራ ዘመም እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ ይካሄድ በነበረው ፀረ ዘውዳዊ አገዛዝ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድረው ነበር፡፡ በአገር ውስጥ ደግሞ እጅግ ጨቋኝ የነበረው ዘውዳዊ አገዛዝና የምዕራባውያን በአገሪቱ ጉዳይ ላይ የነበራቸው ጣልቃ ገብነት በተማሪውና በሙሁሩ ዘንድ የለውጥ ተነሳሽነት ተጽእኖ ማሳደራቸው አልቀረም፡፡ እነዚህ ውጫዊውና ውስጣዊ ሁኔታዎች በጣምራ ኢትዮጵያ ውስጥ የግራ እንቅስቃሴ ቦታ እንዲኖረው የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ እንዲያውም በ1960ዎች የተፈጠሩት እንቅስቃሴዎች ከማርክሲያዊው ርእዮተ ዓለምና የግራው እንቅስቃሴ በሰፊው ተውሰዋል፡፡ በ1960ዎቹ የተመሠረቱት ትላልቅ ፓርቲዎችና ግምባሮች የሶሻሊዝም ጽንሰ ሐሳቦችንና ስትራተጂዎችን በፐሮግራሞቻቸው ውስጥ አካተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥትን በመቃወም ይንቀሳቀሱ የነበሩት የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ /ኢህአፓ/፣ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኤሶን/፣ ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ /ተሓህት/፣ ህዝባዊ ግምባር ሓርነት ኤርትራ

/ህግሐኤ/፣ የመሳሰሉት ድርጅቶች ፕሮራማቸው ውስጥ የግራ አስተሳሰቦችን አስፍረዋል፡፡ በወቅቱ ቀኝ ተብለው የተፈረጁት ፓርቲዎች ሳይቀር ከጊዜው ነፋስ ሊያመልጡ አልቻሉም፡፡ አንዱ ወይ ሌላውን የግራ አስተሳሰብ በፕሮግራማቸው አካተው ነበር፡፡ በወግ አጥባቂ ዓረቦች በእጅጉ ይደገፍ የበረውና የቀኝ መስመር ፖለቲካ አራማጅ ነው ተብሎ ይታወቅ የነበረው ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ /ጀብሃ/ ሳይቀር የግራ አመለካከቶችን በፕሮግራሙ አስፍሮ ነበር፡፡

ከኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ውስጥ ቀድሞ የተቋቋመው ህወሓት ሲሆን ድርጅቱ የመጀመሪያውን ፕሮግራም የነደፈው ማርክሲያዊ ሌኒናዊ ርእዮተ ዓለም መመሪያው እንደሚሆንና ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያልስት አብዮት እንደሚያካሂድ መሠረት በማድረግ ነበር፡፡ በእርግጥ የመጀመሪያው የህወሐት ፕሮግራም የግንባሩን ባህርይ ያገናዘበ እንዳልነበር በብርቱ ይተች ነበር፡፡ ይኸውም ህወሐት የተለያዩ መደቦችንና የፖለቲካ አስተሳሰቦችን ያቀፈ ድርጅት በመሆኑ ራሱን በማርክሲያዊ ሌኒናዊ ርእዮተ ዓለም የሚመራ አብዮታዊ ግንባር አድርጎ ሊወስድ አይችልም የሚል ትችት ነበር፡፡ ድርጅቱ የዚህ ዓይነት ትችትና ሂስ ቢደርስበትም ማርክሳውያን ግለሰቦች በብዛት ያቀፈ ስለሆነ በነዚህ የርእዮተ ዓለሙ አራማጆች ተጽእኖ ሥር ሆኖ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ሊያራምድ ይችላል የሚል ክርክር ያነሣ ነበር፡፡ በመሆኑም በ1971 ዓ.ም በተካሄደው ድርጅታዊ ጉባኤ ባጸደቀው ፕሮግራምም ቢሆን ፀረ-ኢምፔሪያስት፣ ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-በሮክራሲያዊ ከበርቴ ትግሉ እንደሚያራምድ አውጇል፡፡ እንዲያውም ጽንፈኛ የግራ ድርጅት መሆኑን ለማስረገጥ የምዕራብ ኢምፐርያሊስቶች ብቻ ሳዮን ሶብየቶችንም በከላሽነትና በጠላትነት ፈርጇል፡፡ የምዕራቡንና የምሥራቁን ኢምፔሪያሊስት ጎራዎች አበክሮ እንደሚዋጋ አውጇል፡፡

ህወሐት አንደኛ ድርጅታዊ ጉባኤውን ካካሄደ ከአንድ ዓመት በኋላ በአመራሩ ውስጥ ብርቱ የፖለቲካ ክርክር ተነስቶ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የተነሣው አከራካሪ ጉዳይ በሚካሄደው አብዮት የአገራዊው ከበርቴ ወይንምቡርዣ ሚና ምን ይሆናል? የሚል ነበር፡፡ በቻይናና በሌሎች በወቅቱ በሞዴልነት ይጠቀሱ የነበሩት አገሮች የተካሄደው አብዮት አገራዊ ቡርዣውን እንደ ስትራቴጂያዊ ወዳጅ ይወሰድ ነበር፡፡ ለዚህ ሲባል በነዚህ አገሮች የተካሄደው አብዮት «ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት» የሚል ስያሜ ይሰጠው ነበር፡፡ ይኸ ስያሜ የብሄራዊ ወይም የአገራዊ ቡርዣን ሚና ለማጉላት ሲባል የተሰጠ ነበር፡፡ ህወሐት ውስጥ በተካሄደው ፖለቲካዊ ፍጭት ግን ብሄራዊ ቡርዣው

ወላዋይ ስለሆነ የዴሞክራሲያዊ አብዮቱ ስትራቴጂያዊ ወዳጅ ሊሆን አይችልም የሚል ነበር፡፡

ከዚህ ሌላ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ አንድ ፖለቲካዊ ሥርዓት አድርጎ የሚወስድ አመለካከትም ነበር፡፡ በውይይቱ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ራሱን የቻለ የፖለቲካ ሥርዓት ሳይሆን ኋላ ቀር ሥርዓቶችን ለማፍረስ የሚካሄድ ነውጥ መሆኑ ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ህወሐት የተከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ ሶብየቶች በ1917 ዓ.ም የተከተሉት ዓይነት ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚደረግ ነውጥ እንደሆነ ነበር፡፡

ህወሐት ውስጥ የነበሩት «ተራማጆች» በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዙሪያ የሚነሱ በርካታ አንገብጋቢ ጥያቄዎችን አንስተው ከተወያዩና ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ የቀራቸው አንድ ጥያቄ ነበር፡፡ ይኸውም የማርክሲያዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ምሥረታ የተመለከተ ነበር፡፡ ከኢህአፓና ከሌሎች ግራ ድርጅቶች በህወሐት ላይ ይሰነዘር የነበረው ትችት አስተማማኝና ጠንካራ የላብ አደሩ ፓርቲ መሪነት በሌለበት አብዮት ድል አይመታም የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም በ1975 ዓ.ም ከተካሄደው የድርጅቱ ሁለተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ በኋላ ለላብ አደሩ ፓርቲ ቅድመ ዝግጅት እንዲሆን ተብሎ «የግምባር ቀደሞች» -ቨቿነገጭቿረደ.ለጵመጵነተሰ? መሰባሰብ ተጀመረ፡፡ ይህ የግምባር ቀደሞች ስብስብ ለሚመሠረተው የላብ አደር ፓርቲ አስኳል ነበር፡፡ የግምባር ቀደሞች ስብስብ በተለያዩ ፖለቲካዊና ርእዮተ ዓለማዊ ጉዳዮች ዙርያ ውይይቶችን ሲያካሂድ ከቆየ በኋላ በ1977 ዓ.ም ክረምት ላይ ማርክሲያዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ /ማሌሊት/ በሚል የሚታወቀው ፓርቲ ተመሠረተ፡፡ ከዚህ ፓርቲ ምሥረታ በኋላ የግምባሩ ሚና እየደበዘዘ የማሌ ፓርቲው ሚና እየጐለበት ሄደ፡፡ የግምባሩ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም በዚሁ ፓርቲ መሪነት መተግበር ጀመረ፡፡

ማሌሊት ከተመሰረተ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄና/ኢህዴን/ ህዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ ግንባር ፈጥረው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግምባር /ኢህአዴግ/ በሚል ስያሜ ተጠሩ፡፡ ኢህዴን ውስጥ የነበሩት «ግምባር ቀደሞችም» ከማሌሊት ጓዶቻቸው ጋር በመወሃሃድ የኢትዮጵያ ማርክሲያዊ ሌኒናዊ ኀብረትን /ኢማሌኀ/ ፈጠሩ፡፡ የኢህአዴግ ፕሮግራም ይህ ማርክሲያዊ ሌኒናዊ ፓርቲ በሚሰጠው አመራር ሥራ ላይ እንዲውልም ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ በመሆኑም አንድ ወጥ የሆነ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፕሮግራም ሊቀረፅ ቻለ፡፡

ኢህአዴግ በማርክሲያዊ ሌኒናዊ ፓርቲ እየተመራ ሲያራምድ የነበረው የፖለቲካ ፕሮግራም ከሞላ ጐደል የቀደምት ወይንም የሌኒንና የስታሊን እንዲሁም የአልባንያ ኮሚኒስቶች ይመስል ነበር፡፡ እንዲያውም ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲመሳሰል የተደረገው ያልተበረዘ ማርክሲያዊ ርእዮተ ዓለም ያራምዳል ከተባለውና ከአገራችን ሁኔታ ጋር እጅግ ይመሳሰላል ከሚባለው አልባንያ ጋር ነበር፡፡ በመሆኑም እነዚህ ያልተበረዙ ማርክሲስቶች ያራምዱታል የተባለውንና ከሞላ ጐደል ቀደም ሲል የተገለጸውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም ተቀበለ፡፡ በዚህ መሠረትም እስከ 1983 ዓ.ም የሚቀጥሉት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቋሞች በኢህአዴግ ፕሮግራም ውስጥ ሰፍረው ይፋ ሆኑ፡፡

1. የሚቋቋመው መንግሥት የላብ አደሩና የአርሶ አደር አምባገነንነት -ደፀቸተቿተጸረሰሀፀፐ? እንደሚሆን፣
2. የአብዮቱ ምሰሶ የላብ አደሩና የአርሶ አደሩ ቃል-ኪዳን -ጽለለፀቿነቸጽ? እንደሚሆን፣
3. ኢምፔሪያሊዝም፣ ፊውዳሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ከበርቴው የአብዮቱ ጠላቶች እንደሆኑ፣
4. አገራዊ ከበርቴና ከፍተኛ ንኡስ ከበርቴ በወላዋይነት እንደሚፈረጁ፣
5. አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገሪያ ድልድይ እንደሆነ፣
6. ሁሉም መደቦች የላብ አደሩን ግምባር ቀደም መሪነት -ቨቿነገጭቿረደሰሀፀፐ? መቀበል እንዳለባቸውና ያለላብ አደሩ መሪነት አብዮት ድል እንደማይቀዳጅ፣
7. መሬት የህዝብና የመንግሥት ሀብት ሆኖ በመንግሥት እንደሚተዳደር፣
8. የኢምፐሪያሊስቶች ተቋማት ተወርሰው የሰፊው ሕዝብ ሀብት እንደሚሆኑ፣
9. ገዢ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ፣

የሚሉ ነበሩ፡፡

## 3.2 በደርግ ውድቀት ዋዜማና ከደርግ ውድቀት በኋላ የተከለሰው አብዮታዊ ዴሞክራሲ

### 3.2.1 ዓለማዊና አገራዊ ለውጦች በኢህአዴግ አቋሞች ያስከተሉት ተፅእኖ

ደርግ ከመወደቁ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ወይንም ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ኢህአዴግ ውስጥ ከፍተኛ የአቋም መንሸራተት ተከስቷል፡፡ በኢህአዴግ የአቋም መንሸራተት ከፍተኛ ተጽእኖ ከነበራቸው ክስተቶች አንዱም ዓለማዊው የኃይል ሚዛን

እየተለወጠ መሄዱ ነበር፡፡ በምሥራቁ ዓለም በነበረው ሥርዓት ውስጥ በተከሰተው ውስጣዊ ቀውስና የምዕራቡ ዓለም በምሥራቁ ዓለም ላይ ባደረገው ያላሰለሰ ርእዮተ ዓለማዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ዘመቻ ምክንያት የኃይል ሚዛኑ ወደ ምዕራቡ እንዲያጋድል አድርጎታል፡፡ ይህ የኃይል ሚዛን ለውጥ በምሥራቁ ዓለም ከፍተኛ ቀውስ በማስከተል ለመዳከምና ለመበታተን ዳርጎቷል፡፡ ከዚህ የተነሣም በምሥራቁ ዓለም ብቻ ሳይሆኑ የካምፑን ርእዮተ ዓለምና ፖለቲካ ይከተሉ በነበሩና ቅጅውን ባነገቡ ያልበለጸጉ አገሮች ላይም ከፍተኛ ተጽእኖን አስከትሏል፣ ለአንዳንዶችም የውድቀት ምክንያት ሆኗል፡፡ የምሥራቁን ዓለም ርእዮተ ዓለም እንከተላለን በሚሉት ፓርቲዎችና የአርነት ግምባሮች ሳይቀር ተጽእኖው በርትቶ ነበር፡፡ ከነዚህ የላብ አደሩ ርእዮተ ዓለምና አመራር እንከተላለን ከሚሉት ፓርቲዎችና ግምባሮች መካከልም ኢማሌኅና ኢህአዴግ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ኢህአዴግ በደርግ ውድቀት ዋዜማ በተለይ ደግሞ በ1983 ዓ.ም ባደረገው ጉባኤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን ለውጥ መሠረት በማድረግ የፕሮግራም ለውጦችን አካሂዷል፡፡ ካደረጋቸው ለውጦች መካከል ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች 1ኛ/ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የብዙኃን ፓርቲዎች ህልውና ሊቀበል እንደሚችልና 2ኛ/ ከመሪው ማርክሲያዊ ፓርቲ ይልቅ ግንባሩን በማስቀደም መሥራት እንደሚያዋጣ መቀበሉ ነበር፡፡ እነዚህ የአቋም ለውጦች ከምዕራቡ ዓለም ሊደርሱ የሚችሉ ጫናዎችን በማርገብ ረገድ ይረዳሉ ተብሎ የተሳበ ሲሆን በተለይ የማርክሲስ ፓርቲው ከመጋረጃ ጀርባ እንዲተውን የሚያደርገው ውሳኔ በድርጅቱ የፕሮግራም ይዘት ከፍተኛ እንድምታ ማስከተሉ አልቀረም፡፡ ከዚህ ጉባኤ ማግስት ጀምሮ በአባላት ጉባኤ በይፋ የተቋቋመው ማርክሲያዊ ፓርቲ መደበቅ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ህልውናው እንዲጠፋ ተደረገ፡፡ ከኢህአዴግ አርማ በላይ ልቆና ተከብሮ ሲውለበለብ የነበረው ባለ ማጭዱና ማረሻው ቀይ የኢማሌኅ አርማ ከያለበት ተለቀመ፡፡ ይፋዊና ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ለግራ ፖለቲካ ስለማያመቹ ኢማሌኅን ትተን የግንባሩ ዓላማዎችን በማራመድ እንንቀሳቀስ ተባለ፡፡

የኢህአዴግ አመራር ካቋቋመው ማርክሲያዊ ፓርቲ ጋር የተፋታው ውጫዊው ጫና ስለበረታበት ብቻ አልነበረም፡፡ በአገር ውስጥም በሶሻሊዝም ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ተፈጥሯል የሚል ግምት ነበር፡፡ በተለይ ደርግ ይህን ርእዮተ ዓለም አንግቦ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያስከተለው ችግር ታሳቢ ሲደረግ መፈክሩን ይዞ

መንቀሳቀስ የሕዝቡን ጥላቻ መጋበዝ እንደሆነ ይገለጽ ነበር፡፡ በመሆኑም ከሕዝቡ ጋር ስምምነት ለመፍጠር ለዘብ ያለ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫ መከተል ብቸኛው አማራጭ ተደርጎ ተወስዶ ነበር፡፡

ከፍ ብለው የተጠቀሱት ተጽእኖዎች ኢህአዴግ ደርግን አሸንፎ ስልጣን ከመቆጣጠሩ በፊት በፕሮግራሙና ፖለቲካዊ አስተሳሰቡ ላይ ለውጥ እንዲያደርግ አስገድደውታል፡፡ በመሆኑም ያራምደው በነበረ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ ይዘቶች ላይ ለውጦችን አድርጓል፡፡ ሆኖም የተደረጉት ለውጦች በሚገባ ተጠንተውና በጥልቀት ውይይት ተደርጎባቸው የተካሄዱ አልነበሩም፡፡ አመራሩ ከውጭ የሚመጣበትን ጫናና የደጋፊዎቹን አመለካከት ታሳቢ በማድረግ ብቻ የወሰዳቸው እርምጃዎች ነበሩ፡፡

1983 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ ደርግ ከሥልጣን ተወገደ፤ ኢህአዴግም የሥልጣን እርካቡን ተቆጣጠር፡፡ የሥልጣን እርካቡን ከተቆናጠጠ በኋላ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ከፍተኛ ተግዳሮቶች አጋጠሙት፡፡ ካጋጠሙት ችግሮች አንዱም ቀደም ብሎ ይከተለው የነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ አቅጣጫ ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ ጊዜው የበርሊን ግንብ ተንዶ የምዕራቡ ዓለም በምሥራቁ ዓለም ላይ የኃይል ሚዛን የበላይነት የተቀዳጀበትና ሊቨራል አስተሳሰብ ነግሧል ተብሎ የሚነገርበት ስለነበር ኢህአዴግ ቀደም ሲል ያራምደው የነበረውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚል የሚታወቀው የግራ አስተሳሰብ ያለመተዉ አልፎ አልፎ ከሕዝቡ ጥያቄዎችን ማሥነሳቱና  ተጽእኖዎችን ማስከተሉ አልቀረም ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በግራው በተለይ ደግሞ በማሌና በብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የተጠመቁ ካድሬዎችና የኢህአዴግ ደጋፊዎች የፖለቲካ አስተሳሰቡን የሙጥኝ ብለው ይዘው ነበር፡፡ በነዚህ ሁለት ተጻራሪ ክስተቶች የተወጠረው የኢህአዴግ አመራር ከገባበት ችግር ያላቅቁኛል ብሎ የቀየሳቸውን የተለያዩ ድብልቅ ስልቶች ማስፈጸም ጀመረ፡፡

ኢህአዴግ ስልጣን በተቆጣጠረበት ማግሥት በጦርነት የደቀቀውን ኢኮኖሚ መልሶ ለማቋቋም ከፍተኛ ገንዘብ ያስፈልገው ነበር፡፡ በወቅቱ ኢህአዴግ ይህን ገንዘብ ቶሎ የሚያገኝበት መንገድ ከምዕራባውያን መንግስታት፣ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና መንግሥታዊ ካልሆኑት በምዕራባውያን የሚደገፉ ድርጅቶች ስለነበር እነሱን መማፀን ነበረበት፡፡ ሆኖም እነዚህ የገንዘብ ምንጮች ገንዘባቸውን «ከመለገሳቸው» በፊት የሚያስቀምጧቸው ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹም በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ሊቨራል አቅጣጫዎችን መከተል ነው፡፡ በተለይ በምዕራባውያኑ አገራት ተጽእኖ ሥር ያሉት የዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅት ቅድመ ሁኔታዎች

እጅግ ጠንከር ያሉና የማያላውሱ ለዘብተኛ የለውጥ ፓኬጆች መቀበል እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጡ ነበሩ።

ኢህአዴግ ከገባበት ከባድ የኢኮኖሚ መዋጥር ለመላቀቅ ሲል በምዕራባውያን ተቀባይነት ያስገኛሉ ያላቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ለማድረግ ተስማማ። በወቅቱ የምዕራቡ ዓለም ከኢህአዴግ ይጠብቀው የነበረው ዋነኛ የፖለቲካ ለውጥ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ፖለቲካ ፖርቲዎችና ድርጅቶች ያቀፈ የፖለቲካ ሥርዓት ማቋቋም ስለነበረ ይህን የሚያስተናግድ የሽግግር ቻርተር ረቆ እንዲጸድቅ ተደረገ። በሽግግሩ ቻርተር መሠረት የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎችና ድርጅቶች በተቋቋመው መንግሥት እንዲካተቱ ተደረገ። ከአሁን በፊት ከርእዮተ ዓለምና ከፖለቲካ ልዩነት የተነሣ በጎሪጥ ይተያዩ የነበሩና በጦርነት ደም የተቃቡ ድርጅቶች ሳይቀር አንድ ላይ ተሰባሰቡ። የግራ ፖለቲካ አራማጅ የሆነው ኢህአዴግና የባላባት ድርጅት የሚባለው የሱልጣን ዓሊምራሕ ድርጅት አንድ ላይ ተቀመጡ፤ በውግያ ደም የተቀቡት ህወሐትና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኅብረትም/ኢዴኅ/ እንዲሁ አንድ ላይ ተቀመጡ። በጠባብነት ይፈረጅ የነበረው ኦነግም ከዋነኛዎቹ የሽግግሩ መንግሥት መሥራቾች አንዱ ሆነ። ለጋሾች በዚህ እርምጃ ብቻ ባይረኩም የተለያዩ አመለካከቶችን የሚያራምዱ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ የሽግግሩን መንግሥት በመመሥረታቸው በአዎንታ ተመልክተው ለጊዜው ለመልሶ ማቋቋም መርሐ ግብር የሚውል የገንዘብ ድጋፍ አደረጉ።

ምዕራባውያን ለጋሾች ለመልሶ መቋቋሙ መርሐ ግብር የተወሰነ ገንዘብ ቢለግሱም በሥልጣን የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ኢህአዴግ ተጨማሪ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎችን እንዲያደርግ ይወተውቱት ነበር። በተለይ ለልማት የሚውል ብድርና እርዳታ የሚለግሱት የዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅት ኢህአዴግ ሥር ነቀል ለውጦችን እንዲያካሂድ ከባድ ጫና ፈጥረው ነበር። የሚቀርቡለትን ሥር ነቀል ለውጦች ካላካሄደ የዓለም ባንክና የገንዘብ ድርጅቱ መስፈርቶች ስለማያሟላ ብድር ይሁን እርዳታ እንደማያገኝም በግልጽ ተነገረው። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው ኢህአዴግም ተጨማሪ ማሻሻያዎችን ለማድረግ የተቀናጀ የፖሊሲ አቅጣጫ ነደፈ።

በኢህደዴግ አዲስ አስተሳሰብና ትንታኔ ከደርግ ውድቀት በኋላ በአገራችን የፊውዳሉ ሥርዓት ስለተንኮታኮተ በቅሪትነት ካልሆነ በስተቀር እንደ ሥርዓትና እንደ ፖለቲካ ኃይል ሊወሰድ አይችልም። የቢሮክራሲያዊ ከበርቴ ሥርዓት የሚወክለው ደርግ

ስለተደመሰሰም ስጋቱ ቀንሷል፡፡ ቀሪው ጠላት ኢምፔሪያሊዝም ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚያጋጥመው ቀጣይ ፈተና የኢምፔሪያሊስቶችን ጫና ስለሚሆን ይህን የሚቋቋምበትን አቅጣጫ የሚያመለክት ሠነድ በ1985 ዓ.ም አወጣ፡፡ ይህ «አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግቦች እና ቀጣይ እርምጃዎቹ» በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ በድርጅቱ ካድሬዎች መኻል ከፍተኛ ክርክሮችን ያስነሣ ነበር፡፡ የጽሑፉ ዓላማ በአንድ በኩል ያለንበት ዓለም የአንድ ልዕለ ኃያል መንግሥት የበላይነት የተረጋገጠበት ስለሆነ ከዚህ ኃይልና እሱ ከሚመራቸው ተቋማት ጋር እንዴት መሥራት እንደሚቻል ለመጠቆም ሲሞክር በሌላ በኩል ደግሞ አሁንም አብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢህአዴግ የፖለቲካ መመሪያ ሆኖ እንደሚቀጥል ያትታል፡፡ ይህ ሠነድ ኢህአዴግ በሚቀጥሉት ዓመታት የተጓዘበትን አቅጣጫ ያመላከተ ወሳኝ ሠነድ ነበር፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግቦች እና ቀጣይ እርምጃዎቹ የሚለው ጽሑፉ በዋነኛነት ያጠነጠነው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ «ፍፁም የስልጣን የበላይነት» ሐሀቸገጽመጸነየ ጸፈ ፐጸወጽረሐ እንዴት ሊረጋገጥ እንደሚችል አቅጣጫዎችን የሚጠቁም ነበር፡፡ በዚህ ሠነድ መሠረት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርሆዎችና እሴቶች በኅብረተሰቡ እንዲተከሉ ሰፊና የተራዘመ ሥራ እንደሚያስፈልግ ያትታል፡፡ ይህ ከተሳካ ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ ወይንም እንደ ግንባር ቢኖርም ባይኖርም ዓላማው የተሳካ እንደሚሆንና የሕዝቡ ብቸኛ የፖለቲካ ምርጫ ሆኖ እንደሚቀጥል ያትታል፡፡ ሠነዱ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሥር ሰዶ እንዲቀጥል አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎችንም ይጠ ቁማል፡፡

ይኸ ሠነድ ከምዕራባውያን የሚደርሰውን ጫና ማርገብ አስፈላጊ በመሆኑና ከአሁን ወድያ ጨቋኝ መደቦች መልሰው ለማንሰራራትና የአብዮቱ ስጋት ሊሆኑ ስለማይችሉ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የመደራጀት መብት መፍቀዱ አስፈላጊ እንደሆነ ያትታል፡፡ ከዚህ በመነሣት በአገሪቱ ብዙ ፓርቲዎች የሚንቀሳቀሱበት ሥርዓት ህልውና እንዲያገኝ እንደሚደረግ ያውጃል፡፡ ሠነዱ ከዚህ ሌላ በኢኮኖሚው አንዳንድ ተቋማት በመንግሥት እጅ እንዲቀዩና የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ዓላማዎች ለማስፈጽም እንዲያገለግሉ እንደሚደረግ ያትታል፡፡ በዚህ መሠረትም የፋይናንስ ተቋማት፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የምድረ ባቡር ወዘተ. በመንግሥት እጅ እንደሚቆዩ ይገልጻል፡፡ ሆኖም በፋይናንሱ ዘርፍ የአገር ውስጥ ባለሃብቶችም ተሳታፊ እንደሚሆኑ ያትታል፡፡ መሬት በመንግስት እጅ ሆኖ እንደሚቀጥልም ይገለጻል፡፡ ከዚህ በተረፈ ኢኮኖሚው

በገበያ የሚመራ ሆኖ የግል ባለሃብቶችና የውጭ ባለሃብቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ያስረግጣል፡፡

ሠነዱ ለውይይት በቀረበበት ወቅት ሠራዊት በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችም ነበሩ፡፡ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከልም የሠራዊቱ አባላት የኢህአዴግ አባል ሆኖው ቆይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ መድብለ ፓርቲያዊ ሥርዓት ሥራ ላይ ይዋል ከተባለ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም ሠነዱ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ይህ ውሳኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲን አደጋ ላይ አይጥልም ወይ? የሚል ጥያቄም ተነሥቶ ነበር፡፡ ሆኖም ሠራዊቱ የኢህአዴግ አስተሳሰብ ባረፈበት ሕገ መንግሥት ስለሚመራና ቀጥተኛ ያልሆነ የኢህአዴግ አመራር ስለሚያገኝ በዚህ ረገድ  የሚያሰጋ ነገር አይኖርም ተባለ፡፡ ሌላው ይሰነዘር የነበረው አስተያየት አዘል ጥያቄ ኢኮኖሚው በነጻ ገበያ መርህ ከተመራና የግል ባለሃብቱ ሰፊ ቦታ ከተሰጠው አብዮታዊ ዴሞክራሲን  አደጋ ላይ አይጥልም ወይ? የሚል ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ ይሰጥ የነበረው መልስም  ወሳኝ የኢካኖሚ ተቋሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እስከሆኑና በድርጅቶች የሚቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች በመኖራቸው ሊደርስ የሚችለውን ተጽእኖ ሊቀንሰው ይችላል የሚል ነበር፡፡ ጽሑፉ ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማው የበላይነት ተቀዳጅቶ ሊቀጥል የሚችለው በዋነኛነት የአርሶ አደሩ ድጋፍ አግኝቶ መጓዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ ሌላም ላብ አደሩና የከተማው ንኡስ ከበርቴ ከአብዮቱ ተጠቃሚዎች ናቸው፣ ወዳጅ ሆኖ ሊቀጥል የማይችለው አገራዊ ቡርዧውም ቢሆን የነጻ ገበያው ተጠቃሚ ሆኖ አብዮቱን እንዳይጻረር ማድረግ እንደሚገባ ያትታል፡፡ ጽሑፍ የአብዮቱ አደጋ ከተማ ውስጥ እንደሆነ ይጠቁማል ሆኖም ከተማ ውስጥም ሰፊውን ህዝብ በተለያዩ ማኅበራት በማደራጀትና እነዚህን ማኅበራት በመቆጣጠር ድጋፍ ማግኘት እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ ኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፕሮግራሙን በማስፈፀም ረገድ ከላይ የተጠቀሱትን አቅጣጫዎች እንደሚያስፈጽም ይግለጽ እንጂ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የተስማማባቸው ሠነዶች ሲመረመሩ ግን የዚህ ተፃራሪ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በተለይ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ጋር ያደረገው ስምምነት በአገሪቱ ሊቨራል ርእዮተ ዓለም ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የሊቨራል አስተሳሰብ መሠረት ያደረጉ ሦስት መሠረታዊ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ተሰማምቷል፡፡ እነዚህ ማሻሻያዎችም 1ኛ/ ኢኮኖሚው በነጻ ገበያ መርህ እንዲመራና ለውጭ ባለሃብቶች ክፍት እንዲደረግ -ለፀበጽረቷለፀዘቷተፀጸነ? 2ኛ/ በመንግሥት

ቁጥጥር ሥር ያሉት የንግድና የማምረቻ ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ -ፐረፀሸቷተፀዘቷተፀጸነ? 3ኛ/ በኢኮኖሚ በአጠቃላይ መሠረታዊ የመዋቅር ለውጥ እንዲደረግ -ርጵሰተረጭቸተጭረፀነገ? የሚሉት ናቸው፡፡ ዋነኛው የስምምነት አቅጣጫ ይህ ሆኖ እያለ ግን አንዳንድ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው ቀጥለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህም ቢሆኑ ቀስ በቀስ ወደ ግል እንደሚዘወሩና የውጭ ባለሃብቶች ሊሰማሩባቸው እንደሚችሉ ታሳቢ ያደረገ አካሄድ ነበር፡፡ እንግዲህ በኢኮኖሚ ዘርፍ እነዚህ የማሻሻያ ለውጦች ከተደረጉ ሊቨራል የኢኮኖሚ አቅጣጫ ምን ያህል ሥር እንደሰደደ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ በፖለቲካዊ መስክም የሊቨራል አስተሳሰብ እንዲቀበልና መመሪያው አድረጎ እንዲወስደው ከፍተኛ ተጽእኖ ደርሶበታል፡፡ በዓለም አቀፍ ተቋሞቹ ኢኮኖሚው በሊቨራል አቅጣጫ እየተጓዘ ፖለቲካው ይህን ካላንጸባረቀ የዕድገት ማነቆ ይሆል የሚል ጠንካራ ትችት ይሰነዘር ነበር፡፡ ከዚህ የተነሣም ኢህአዴግ በፖለቲካ ፕሮግራሙ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደሚያራምድ ሲያውጅ በሕገ መንግሥቱ ግን መሠረታዊ የሊቨራል አስተሳሰቦች የሚያንጸባርቁ አንቀጾችና ክፍሎች እንዲካተቱ አድርጓል፡፡

### 3.2.2. *ከ1993 ዓ.ም የኢህአዴግ ቀውስ በኋላ የተደረጉ ተጨማሪ ለውጦች*

በ1993 ዓ.ም ኢህአዴግ ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ እንደተከሰተ ይታወሳል፡፡ ቀውሱ ክፉኛ ያናወጠው ደግሞ የኢህአዴግ አንጋፋ መሥራች የሆነውን ህወሓትን ነበር፡፡ ህወሓት በተፈጠረው ቀውስ ለሁለት ተከፍሏል፡፡ ድርጅቱ ለሁለት ከመከፈሉ በተጨማሪ በኢህአዴግ አስተሳሰብ በተለይ ደግሞ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሐሳብ ላይ ያስከተለው ተጽእኖ ከፍተኛ ነበር፡፡ በቀውሱ አፍላ ጊዜያት ላይ በአቶ መለስ የሚመራው ቡድን ሁለት ተጻራሪ የሚመስሉ ስልቶችን ተከትሎ ነበር፡፡ እነሱም ምዕራባውያን መንግሥታትና ባለ ሃብቶችን ለመሳብ የተቀየሱ ስልቶችና ካድሬውንና አርሶ አደሩነ ለመሳብ የተቀየሱ ስልቶች ነበሩ፡፡ ለምዕራባውያንና ለባለሃብቶች ይሰጡ የነበሩ መግለጫዎች አፈንጋጮች ኮሚኒስቶች፣ ግራ አክራሪዎች እንዲሁም ብሄርተኞች ናቸው የሚል ሲሆን ለካድሬዎችና ገበሬዎች ይሰጡ የነበሩ መግለጫዎች ደግሞ አፈንጋጮች አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሚጻረሩ ጥገኞች፣ ጠባቦች፣ ሙሰኞች፣ ፀረ-ዴሞክራቶች ወዘተ. ናቸው የሚሉ ነበሩ፡፡ አጠቃላይ የጉዞው አቅጣጫ በአንድ በኩል

ምዕራባውያን ዲፕሎማቶችና ተቋሞቻቸው ለማርካት ሲባል የቀኝ ፖለቲካ አቀንቃኝና አፍቀሬ ሊቨራላዊ አስተሳሰብ መስሎ መታየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የካድሬዎችን ቀልብ ለመሳብ አብዮታዊ መስሎ መታየት ነበር፡፡ እንዲያውም ነገሩን ለማመሳቀል ሲባል ለዓመታት የተረሳው የነማርክስ መጻሕፍት ከተቀበሩበት ወጥተው የነ ሉዊ ቦናፓርቲ ታሪክ ተዘክሮ ለማቅረብ የተሞከረበት ሁኔታ ነበር፡፡

ይኽ ሙከራ የሚፈለገውን ቀውስ የማርገብ ተልእኮውን ካሳካ በኋላ ምርጫ 97 ተቃረበ፡፡ ይህ ምርጫ እንከንየለሽና ፍጹም ዴሞክራሲያዊ ይሆናል የሚል አዋጅ ተነገረ፡፡ በኢህአዴግ ግምገማ ተቃዋሚዎች ፈጽመው ሊያቸንፉ ስለማይችሉ የፖለቲካ ምኅዳሩን ለቀቅ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል አቅጣጫን ተከተሉ፡፡ ይኽ ክስተት ገዥው ፓርቲ በአንድ በኩል ተሃድሶው በእርግጥም ሰፊ መብቶችን እንደሚያስጨብጥና ዴሞክራሲ እንዲያብብ የሚያደርግ መሆኑን ለመስበክ የተጠቀሙበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎች አጋጣሚውን እንዲጠቀሙት በር የከፈተ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ሰፊ ድጋፍ አሰባሰቡ፡፡ የኢህአዴግን በትረ ሥልጣንም እንዲነቃነቅ አደረጉ፡፡ በዚህ ጊዜ እውነተኛው የኢህአዴግ ባህሪ ተከሰተ፡፡ የውስጥ ተቀናቃኞችን ያለምህረት የጨፈጨፈውና ያስወገደው ኢህአዴግ በተቃዋሚዎችና ደጋፊዎቻቸው ከባድ ዘመቻ አወጀ፡፡ ከፍተኛ ወከባ እስርና ግድያ በመፈጸም ሁኔታውን ለማረጋጋት ሞከረ፡፡

ኢህአዴግ ምረጫ 97ን ተከትሎ በድንጋጤ የወሰዳቸው እርምጃዎች ዘላቂ ማስታገሻ ሊሆኑ እንደማይችሉ በመገንዘቡ በንድፈ ሐሳብ የተደገፉና ተቀባይነት -ልጽገፀተመቷቸየ? ሊያገኙ የሚችሉ እርምጃዎች መውሰድ እንደ አማራጭ መውሰዱ ተገቢ መሆኑን ተገነዘበ፡፡ ለዚህ የመረጠው ስልትም አብዮታዊ ዴሞክራሲን ዳግም እንዲከለስ በማድረግ ለአፈናና ቁጥጥር ይበልጥ እንዲመች አድርጎ መቀመሩን ነው፡፡ በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በተመለከተ በርካታ ሠነዶች በተከታታይ ተዘጋጁ፡፡ በዚህ ዙሪያ ከተዘጋጁ ሠነዶች መካከል አራቱ ተጠቃሾች ናቸው እነሱም፡-

1ኛ/ ልማት፣ ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ -ጥቅምት 1999ዓ.ም?

2ኛ/ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስትራቴጂ፣ ታክቲኮችና የአመራር ጥያቄ፣ -ጥቅምት 1999ዓ.ም?

3ኛ/ የአፍሪካ ልማት፣ ተስፋ ቢሱ ጉዞና አዲስ ጅማሪ፣

4ኛ/ አገራዊ ለውጦች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሔዎች፣ -ሰኔ 2000 ዓ.ም? የሚሉ ናቸው::

በነዚህ ሠነዶች የሰፈሩት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰቦች ቀደም ሲል ሶቭዮቶችና ኮሚኒስት ኢንተርናሽናል ኋላ ላይ ደግሞ ህወሐት/ማሌሊት ይከተሏቸው ከነበሩት በመሠረቱ የተለዩ ናቸው:: አልፎ አልፎም በነዚህ ሠነዶች የሚገለጹት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሐሳቦች መሠረታዊ ልዩነቶች ይታዩባቸዋል::

ኢህአዴግ በነዚህ ሠነዶች የቀመረው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገሪያ ድልድይ አድርጎ አይወስደውም:: እንዲያውም ወደ ሊቨራል ዴሞክራሲ ለመሸጋገር አስፈላጊ ሂደት አድርጎ ያቀርበዋል:: ገና ባልዳበረ እንደኛ ዓይነቱ አገር ሊቨራል ዴሞክራሲ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችልና ተግባራዊ ይሆን ዘንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንደ ማሸጋገሪያ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልጻል:: ይህ ደግሞ ከዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በመሠረቱ የሚለይ ብቻ ሳይሆን ፍፁም የሚጻረር ነው:: የኢምፔሪያሊስቶችንና የፊውዳሎችን ሥርዓት በማፈራረስ ወደ ሶሻሊዝም ያሸጋግራል የተባለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የቡርዣው ሥርዓት አንጹ መልክ ወደ ሆነው ወደ ሊቨራል ዴሞክራሲ መሸጋገሪያ ይሆናል ማለት ከዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንጻር ሲታይ ስህተት ብቻ ሳይሆን ፊዝም ጭምር ነው::

ሌላው የዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ይዘት የላብ አደሩና የአርሶ አደሩ ጣምራ አምባገነንነት የሚያረጋግጥ መሆኑ ነው:: በቅርቡ እየወጡ ባሉት የኢህአዴግ ሠነዶች ላይ ግን ላብ አደሩን ወደ ጐን በመተው አርሶ አደሩን መሠረት ያደረገ የንኡስ ከበርቴው የበላይነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት መሆኑን ይገልጻል:: ብቅርቡ ደግሞ ከገበሬው መኻልም ዋናው ኃይልና መሪ ተዋናይ «ሀብታም አርሶ አደር» እንደሆነ ይፋ ሆኗል:: ይህም በዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ታሪክ ጭራሽ ተሰምቶ የማያውቅ ነው::

በኢኮኖሚው መስክም ዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢምፔሪያሊስቶችን ሀብት በመውረስ ጠንካራ መንግሥታዊ የኢኮኖሚ ዘርፍ በተለይ ደግሞ የኢንዲስትሪ ዘርፍ እንዲኖር ያደርጋል:: የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግን በፕሮግራም ደረጃ ያለንበት ዘመን የግሎባላይዘሽን ዘመን ስለሆነ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር መቃቃር ሳይሆን ከእነርሱ

ጋር ትስስር መፍጠር ብቸኛው መንገድ ነው ይላል፡፡ ስለሆነም ከግሎባላይዘሽን ኃይሎች ጋር ቁርኝት በመፍጠር እነሱ የሚፈጥሩልህን ልዩ ዕድል መጠቀም ተገቢ ነው ይላል፡፡ የአገሮች የዕድገት ልዩነት ከመወጣጫ መሳልል ጋር በማመሳሰል በዝቅተኛው የመሳልል እርከን ያሉት አገሮች በእርከኖች እየተንጠላጠሉ ደረጃቸውን ማሻሻል አለባቸው ይላል፡፡ ይህም ከመሠረታዊውና ዓይነተኛው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ያፈነገጠና ጭራሽ ተጻራሪ የሆነ ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡

ዓይነተኛው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ራሱን የቻለ ሥርዓት ባይሆንም በዓላማ ደረጃ ግን የተመዘበሩና የተጨቆኑ መደቦችን ለመጥቀም የቆመ ነው፡፡ ስለሆነም የአገር ሀብት በመንግሥትና በሕዝብ እጅ አስገብቶ «ፍትሐዊ» የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ ወደ የሶሻሊስት ሥርዓት ለመረማመድ ይሞክራል ፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ግን ይህን ይጻረራል፡፡ በመሬት ድልድል አማካኝነት ገበሬውን እጠቅማለሁ ቢልም ዞሮ ዞሮ ለመጥቀም የተነሳው ግን የተሻለ ዓቅምና ሀብት ያለውን ሀብታሙን ገበሬ መሆኑ በይፋ አውጇል፡፡ እንዲያውም የፖለቲካ መሪነቱ ጭምር መጨበጥ ያለበትም ሀብታም ገበሬ እንዲሆነ አስረግጧል፡፡ በመሆኑም የኢህአዴግ ፖሊሲ የሚያጠነጥነው ሀብታም ገበሬን በመጥቀምና በመደገፍ ዙሪያ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የከተማው ድሃ የኅብረተሰብ ክፍል ከሚፈጠሩት የኢኮኖሚ ተቋሞች ትርፍራፊ በመለቃቀም ኑሮውን የሚያሻሽልበትን እንጂ የተለየ የቀረፀው ፖሊሲ የለውም፡፡ በዚህ ረገድም ከዓይነተኛው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ይለያል፡፡

## 4. <u>የኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መሠረታዊ ችግሮች</u>

የኢህአዴግ የፖለቲካ ችግሮች በተናጠል መመልከት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማፈላለግ ረገድ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል፡፡ ችግሩ ሥር የሰደደ የአመለካከት ተቋማዊ አወቃቀርና እነዚህን ተከትሎ የሚራመደው የአገዛዝ ዘይቤ ውጤት መሆኑን ካልተገነዘቡ የሚደረጉት እንቅስቀሴዎች ሥር ነቀልና ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመሆኑም የችግሩ ምንጭ የሆኑትን የሥርዓቱ መሠረታዊ አስተሳሰቦችና አቅጣጫዎችን በመገንዘብ መፍትሔ ማፈላለግ ያሻል፡፡ የኢህአዴግ ችግሮች የሚመነጩት እየተከተለ ካለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ አስተሳሰብና አቅጣጫ መሆኑ በመገንዘብ መፍትሔችን መሻት ተገቢ በመሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

4.1 <u>ከፖለቲካ አንጻር የሚነሡ ችግሮች</u>

4.1.1 <u>የአንድ ፓርቲ ሥርዓት ለመፍጠር ያለመ አቅጣጫ</u>

ኢህአዴግ የሚመራው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በይፋ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የበላይነት -ሀጵገጵመጸነየ? የሚያረጋግጥ ሥርዓትና አስተሳሰብ ለመመሥረት እንደሚሠራ አውጇል። ይህ አካሄድ መድብለ ፓርቲና መድብለ ሃሳብን የሚጻረር ነው። ከዚህ ሌላም የአንድ ፓርቲ ፍፁም የበላይነትን በማረጋገጥ አምባገነናዊ ሥርዓት እንዲቋቋም ያደርጋል። የአገራችን ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ መድብለ ፓርቲና መድበለ ሃሳብ የሚቀበል ሥርዓት እንደሚኖር ቢያመለክትም የኢህአዴግ ሠነዶች የሚያመለከቱት ግን የዚህ ተጻራሪ ነው። የኢህአዴግ ሠነዶች ለኢትዮጵያ ልማት፣ መረጋጋትና ዴሞክራሲ ብቸኛው ዋስትና አብዮታዊ ዲሞክራሲ እንደሆነ ይገልጻሉ። የፓርቲው ቁንጮ አቶ መለስም ሊቨራል ዴሞክራሲ ተፈትኖ የወደቀ የፖለቲካ አቅጣጫ እንደሆነ በይፋ አውጀዋል። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የአንድ ፓርቲ አገዛዝ እንደሆን የሚያመለክ ነው።

እንዲያውም አሁን አሁን በምስራቁ ይሁን በምዕራቡ ዓለም በአንድ ፓርቲ ወይም በአንድ የፓርቲዎች ስብስብ -ቸጸቷለፀተፀጸነ? ለአሥርት ዓመታት የተገዙ አገሮች መኖራቸውን በአብነት በመግለጽ ግዛታቸውን ዘለዓለማዊ ለማድረግ እንደሚፈልጉ እየነገሩን ነው። ጃፓን ውስጥ አንድ ኮሊሽን ለ50 ዓመታት ያህል እንደገዛ፣ ስዊድን ውስጥ አንድ ፓርቲ ከ40 ዓመታት በላይ በሥልጣን እንደቆየ እየገለጹልን ነው።

የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ለአገራችን አግባብነት እንዳለው ከሌላ አቅጣጫም ሊነግሩን ይፈልጋሉ። በአንድ አገር ያለው የኢኮኖሚ ችግር በአንድ የምርጫ ዘመን መፍትሔ ሊያስገኝ እንደማይችልና ፓርቲያቸውም ረዘም ያለ የግዛት ዘመን ካላገኘ ለውጥ ለማምጣት እንደማይችል እየገለጹልን ነው። እርግጠኞች ለመሆንም ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ወዳላት አገር ለማሸጋገር ከ20 እስከ 30 ዓመታት እንደሚያስፈልግ እየገለጹ ነው። ይህን ለማድረግም ፓርቲያቸው ካሳለፈው 18 ዓመታት በተጨማሪ ቢያንስ 20 አልያም 30 ዓመታት እንደሚያስፈልገው እየገለጹ ነው። 38 ወይም 48 ዓመት በአሁኑ ጊዜ የዜጎች መካከለኛ ዕድሜ እየሆነ ነው። እንደሚታሰበውም ለውጥ በማምጣት ሽፋን ኢህአዴግ ለ38 ወይም 48 ዓመት በብቸኝነት መግዛት ይኖርበታል።

ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለውም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ መጫን ሲቻል ብቻ ነው::

4.1.2 ተቃዋሚን በጠላትነት የሚፈርጅ አቋም

ጠላት የሚለው አገላለፅ በጥንቃቄ ካልታየ አደገኛ ነው:: በተለምዶ ጠላት የሚለው ቃል የአንድን አገር ሉአላዊነትና ጥቅም ለማጥፋት ለሚነሣ የውጭ ኃይል ወይንም መንግሥት የሚሰጥ ስያሜ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የአገሩን ጥቅም ለውጭ ኃይሎች አሳልፎ የሚሰጥ ቅጥረኛም በጠላትነት ሊፈረጅ ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ በአንድ አገር ያሉን ዜጎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ቡድኖች በጠላትነት ሊፈረጁ አይችሉም፡፡ የመደብ ትግል እናካሂዳለን የሚሉ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ኃይሎች ግን ኅብረተሰቡን በመደብ በመከፋፈል በጠላትና በወዳጅ ጎራ ይከፋፍሉታል፡፡

ኢህአዴግ የመደብ ትግል የሚያካሄድ ድርጅት እንዳልሆነና ይህን አቋሙን እርግፍ አድርጎ እንደተወ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ እንዲያውም ከአሁን በፊት ኢምፔሪያሊስቶች፣ መሳፍንቶችና ቢሮክራሲያዊ ከበርቴዎች በማለት በጠላትነት ይፈረጃቸው የነበሩን ከደርግ ውድቀት በኋላ በጠላትነት እንደማይመለከታቸው ሠነዶቹ ይመሰክራሉ:: አሁን ደግሞ ካለው ዓለማዊ ትስስር የተነሳ ኢምፔሪያሊስት ይላቸው ከነበሩ ኃይሎች ጋር በመተሳሰር ካልሆነ በስተቀር በመቆራረጥ ዕድገት ሊመዘገብ እንደሚይቻል ሠነዶቹ ይገልጻሉ:: በአገር ውስጥም የከበርቴውን መደብ በጠላትነት እንደማይፈርጀው ደጋግሞ ይገልጻል:: ግፋ ቢል ከበርቴውን ወላዋይ ነው ይለዋል:: ከዚህ አንጻር ሲታይ ኢህአዴግ በመደብ ጠላትነት የሚፈረጀው ኃይል የለውም::

ኢህአዴግ አገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ጥቅም የሚንዱ የውጭ ፓርቲዎች ወይም በውጭ መንግሥታት የሚሽከረከሩ ቅጥረኞች እንዳልሆኑም ያውቃል:: ያ ቢሆን ኖሮ ሕጋዊ ፈቃድም ባልሰጣቸውም ነበር:: ከዚህ የተነሣም በውጭ ኃይልነት ወይንም የውጭ ኃይል ቅጥረኝነት ሰበብም በጠላትነት ሊፈረጁ እንደማይችሉ ግልጽ ነው:: እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጥገኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ ጠባቦች፣ ትምክህተኞች፣ ወዘተ. በማለት በጠላትነት ይፈርጃቸዋል:: ኢህአዴግ እነዚህን ፓርቲዎችና ኃይሎች በጠላትነት የሚፈርጃቸው በፖለቲካው ውድድር ሕዝቡ ጠላቶች ናቸው በማለት ድምፅ እንዳይሰጣቸውና ተወዳድረው ቢያሸንፉት ደግሞ ጠላቶች ናቸው በማለት በኃይል ለመምታትና ለመጨቆን ያስችለኛል በማለት ነው:: ይህን የሚያደርገው ለረጅም ጊዜ ያለ ማንም ተቀናቃኝ በአምባገነንነት ለመግዛት ካለው

ፍላጎት የመነጨ ነው:: ካልሆነማ የአገር ውስጥ የፖለቲካ ኃይሎችና ፓርቲዎች የተሳሳተ አቋምና አቅጣጫ የከተላሉ ከማለት ውጭ በጠላትነት ባልተፈረጁ ነበር:: ከዚህ አንጻር የተሳሳተ ፖሊሲና የተለየ ችግር ያለባቸውን ፓርቲዎች የመለየት መብት ደግሞ የመራጩ ሕዝብ ፋንታ እንጂ የኢህአዴግ ሊሆን ባልተገባ ነበር::

4.1.3 __የመንግሥት አካላት አንዱ ሌላውን የመቆጣጠር መርህ የሚጻረር አካሄድ__

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንድ የመንግሥት አካለ ሌላውን በመቆጣጠር መርህ ላይ የተመሠረተ ነው:: ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ ነጻነታቸው ተጠብቆ አንዱ ሌላውን ይቆጣጠራል:: ዜጎች ቀልጣፋና ፍትሐዊ አስተዳደር የሚያገኙት በዚህ መርህ ላይ የተመሠረተ መንግሥታዊ አወቃቀርና አሰራር ሲኖር ነው:: የአንዱ አካላ በሌላው ጣልቃ መግባትና ተጽእኖ ማሳደር ካለ ፀረ ዴሞክራሲ ተግባር እየሆነ ነው:: ከዚህ አንጻር ሲታይ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአንድ ፓርቲና በአንድ ርእዮተ ዓለም መሪነትና የበላይነት የሚያምን ነው:: በመሆኑም ሦስቱ የመንግሥት አካላት በአደረጃጀት ደረጃ ቢለያዩም ቀጥታዊና ቀጥታዊ ያልሆነ መመሪያ የሚያገኙት ግን ከአንድ የዕዝ ማዕከለ ነው::

በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነትና አሠራር ሥልጣን በአንድ ማዕከል ሥር የተሰባሰበ ነው:: የፓርቲ ማዕከላይ ኮሚቴ በፓርቲው መዋቅር ከፍተኛ ሥልጣን ይኖረዋል:: ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ደግሞ ከማእከላይ ኮሚቴ በላይ የበለጠ የማስፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል:: የዚህ አካል አባላት ገዥ ፓርቲ የመሆን ዕድል ካገኙ በአገሪቱ ወሳኝ በሚባሉ የመንግሥት አካላት በሙሉ ስለሚሰማሩ በተለይም የመንግሥት የአስፈጻሚ አካል አባላት ሆነው ስለሚመረጡ በሌሎች የመንግሥት አካላት ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖራቸዋል:: የተለያዩ የመንግሥት አካላትን የዕለት ተዕለት የሥራ ሂደት በመምራት የሚያሽከረክሩት እነዚህ የሥራ አስፈፃሚ አባላት ናቸው:: በሕገ መንግሥት ደረጃ ፓርላማው የበላይ ሥልጣን መሆኑ ቢታወጅም የሚወስናቸው ውሳኔዎች ሁሉ በፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ መመሪያ መሠረት ነው::

የሥራ አስፈጻሚ ፈላጭ ቆራጭ ለመሆኑ ምሳሌ የሚሆነው የሕግ አወጣጥ ሂደቱ አንዱ ነው:: ማንኛውም ሕግ ለፓርላማ የሚቀርበው በሥራ አስፈፃሚው አካል ከታየና ከተመረመረ በኋላ ነው:: የሕግ ረቂቅ ሐሳብ ከፓርላማ አባላት ወይም ከህዝቡ ሊፈልቅ ከቶ አይችልም:: የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚው ደግሞ በፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ አባላት የተተበተበ ነው:: በመሆኑም ፓርላማው ለይስሙላ ነጻ ነው ቢባልም በተጨባጭ

በሥራ አስፈፃሚው አካል ቁጥጥርና ተጽእኖ ሥር ነው፡፡ የሥራ አስፈጻሚው አካል በፍትሕ ሥርዓቱም ከፍተኛ ተጽእኖና ቁጥጥር አለው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በቀጥታ በሥራ አስፈፃሚው ሥር ሲሆን የዳኞችን ሹመትና ዲሲፒን የሚቆጣጠረው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤም በሥራ አስፈጻሚ በሚሾሙ ግለሰቦች የተሞላ ነው፡፡ በመሆኑም ዳኞች ሥራቸውን በነጻነት ማከናወን ይችላሉ ቢባሉም ከሥራ አስፈጻሚው ተጽእኖ ከቶ ነፃ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡

### 4.1.4 <u>ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን የሚገድብና አምባገነንነትን የሚያጠናክር ፖለቲካ</u>

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ኅብረተሰቡ ውስጥ ካሉት መደቦች መካከል ለገበሬው በተለይ ደግሞ ለሀብታም ገበሬው እንደሚቆም ይገልጻል፡፡ ከሀብታም ገበሬው ጐን ሊቆሙ የሚችሉ ሌሎች አጋር መደቦች ይኖራሉ ቢልም በጠላትነትና በመኻል ሰፋሪነት የሚፈርጃቸው መደቦችና ወገኖች እንዳሉም ይገልጻል፡፡ አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ወይንም ቡድን በጠላትነት አልያም በመኻል ሰፋሪነት ከተፈረጀ ደግሞ ወዳጅ ከሚባሉት መደቦቹና ኃይሎች እኩል የዴሞክራሲ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በቀድሞው አገላለፅ የላብ አደሩና የአርሶ አደሩ አምባገነንነት በአሁኑ አገላለጽ ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የበላይነት ታሳቢ ሲደረግ መብታቸው የሚገደብና በጠላትነት የሚታዩ ወገኖች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ ይህም በዴሞክራሲያዊና በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ ተጽእኖን የሚያሳድር ነው፡፡

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አሁንም በተደጋጋሚ በጠላትነት የሚፈረጃቸው የፖለቲካ ኃይሎችና ድርጅቶች አሉ፡፡ ጠባቦች፣ ትምክህተኞች፣ ጥገኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች ብሎ የሚፈርጃቸው ወገኖች በጠላትነት ይፈረጃሉ፡፡ በጠላትነት መፈረጃቸው ብቻም ሳይሆን የተለያዩ የዴሞክራሲያዊ መብቶች አፈናና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ይደርስባቸዋል፡፡ ሕገ መንግስቱ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንደከበሩ ቢደነግግም በርካታ ወገኖች የዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሰለባዎች ሆነዋል፡፡

ኢህአዴግ በተለያዩ ወቅቶች ፈተናዎች ሲያገጥሙት ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ለመገደብ እንደሚሞክር በተለያዩ አጋጣሚዎች ታይተዋለ፡፡ ዜጎች ጠንከር ያሉ ተቃውሞችን ሲያሰሙ የቀይ መብራትና የፈንጂ ወረዳ ማስጠንቀቅያዎች ይሰጣሉ፡፡ በቀይ መብራትና በፈንጆ ወረዳዎች የታጠሩ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ደግሞ

ሊያስከትሉት የሚቸሉት ችግር ግልጽ ነው፡፡ ዜጎች ራሳቸው መብቶቻቸውን ከመጠቀም እንዲቆጠቡ ሊያደርጉ ይችላሉ ወይንም ደግሞ የጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ክስተቶች በአገራችን በተደጋጋሚ ታይተዋል፡፡

በአንድ አገር የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተረገጡ የማደረጉት ምርጫዎች ዓለም ዓቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟሉ አይሆኑም፡፡ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ሊካሄድ አይቻልም፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተረግጠው ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ደግሞ የይስሙላ ምርጫ ቢካሄድም አምባገነንነት ከማጠናከር ያለፈ ሊሆን አይችልም፡፡ በአገራችን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው፡፡

4.1.5 ***የፖለቲካ ምኅዳሩን የሚያጠብ አካሄድ***

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ /የሥልጣን/ የበላይነቱን ለማረጋገጥ የሚወስዳቸው እርምጃዎች የፖለቲካ ምኅዳሩን እጅግ ያጠቡታል፡፡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ተቋማት ሲዘጉና ሲገደቡ የዜጎችን ነጻነቶች የሚገድቡ ሕጎች ሲፀድቁ የፖለቲካ ምኅዳሩ ይጠባል፡፡ ከመርህ የመነጨ ሳይሆን ለታይታ ሲባል በምርጫ 97 ዓ.ም ትንሽ ለቀቅ የተደረገው የፖለቲካ ምኅዳር በምርጫው ማግስት እጅግ እንዲጠብ ተደርጓል፡፡

በ1997 ዓ.ም ለኢህአዴግ ሽንፈት አስተዋጽኦ አድርገዋል ተብለው የተገመቱት የፕሬስና የሲቢል ማኅበረሰብ ተቋማት አዲስ በፀደቁትና በረቀቁት ሕጎች አማካኝነት እንቅስቃሴያቸው እንዲገደብ እየተደረገ ነው፡፡ በፕሬስ ሕጉ መሰረት ጋዜጠኞች፣ አሳታሚዎች፣ አከፋፋዮች ካጠፉ ይደርስባቸዋል የተባለው ቅጣት እጅግ ከባድ ከመሆኑ በላይ የከፉ ወንጀሎች ለተባሉት ከተደነገገው ቅጣት በላይ መደንገጉ እንደ ማስረጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ የባሰው ግን ገዢው ፓርቲ ፕሬሶችን በጠላትነት የሚመለከታቸው መሆኑ ነው፡፡

የሲቭል ማኅበረሰባትንም እንዲሁ እንቅስቃሴያቸው እንዲገደብ የሚያደርግ ሕግ ረቋል፡፡ ሲቭል ማኅበረሰባት ከተቃዋሚዎች ጋር ወግነዋል የሚል የኢህአዴግ ግምገማ ስላለ እነዚህን ለማዳከም አዲስ ሕግ እንዲረቅ ተደርጓል፡፡ ሲቭል ማኅበረሰባትን በገንዘብና በአስተዳደራዊ አግባብ ለማሽመድመድ የተረቀቀው ሕግ አሁንም ፖለቲካዊ ምኅዳሩን የሚያጠብ እርምጃ ነው፡፡

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፕሬስንና ሲቭል ማኅበረሰባትን ሲያስብ በእሱ ሥር እንደሚሆኑ ታሳቢ ያደረገ እንጂ ከልብ በነጻነት እንዲደራጁ የማይፈቅድ ስለሆነ የተወሰነ ተነጻጻሪ ነጻነት በሚያሳዩበት ወቅት ሲያዋክባቸውና ሲያሳድዳቸው ታይቷል፡፡ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ እንዳይሠሩ በሕግ ሊቆጣጠራቸው እየሞከረ ነው፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንዱ ችግርም እያንዳንዱን ተቋም በመቆጣጠር አጠቃላይ ፖለቲካዊ ምኅዳሩን ለማጥበብ የሚንቀሳቀስ መሆኑ ነው፡፡

4.1.6 <u>እያንዳንዱን ዜጋ በመቆጣጠር ኅብረተሰቡን ለመቆጣጠር መሞከር</u>

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እያንዳንዱን ዜጋ በሁለት መንገድ ለመቆጣጠር ይሞክራል፡፡ አንዱ የመቆጣጠርያ ዘዴ ዜጎችን በተለያዩ አደንቋሪ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻዎች ለማጥመቅ -ፀነደጸቸተረፀነቷተጵ? ለማድረግ መሞከር ሲሆን ሌላው ደግሞ በድርጅታዊና አስተዳደራዊ መንገድ ለመቆጣጠር መሞከር ነው፡፡

ዜጎችን የማጥመቁ ዘዴ በመንግሥት ሚድያዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በቀበሌ መዋቅሮችና በስብሰባዎች ወዘተ. አማካይነት የሚካሄድ ነው፡፡ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ነጋ ጠባ ኢህአዴግና እሱ የሚመራው መንግሥት ፖሊሲዎችና አስተሳሰብ በማሰራጨት ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ በዜጎች አንጡራ ሀብት የተቋቋሙት መገናኛ ብዙሃን የአንድ ፓርቲ ርእዮተ ዓለምና ፖለቲካዊ መስመር ማሰራጫ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ትምህርት ቤቶችም ከላይ እስከ ታች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተ ዓለም እንዲያስተጋቡ እየተቀረጹ ነው፡፡ እያንዳንዱ አስተማሪ የኢህአዴግ አባል እንዲሆን ሲወተወትና ሲገደድ ዓላማው እሱን በመሣሪያነት ተጠቅሞ ተማሪዎችን ለማጥመቅ ነው፡፡ ተማሪዎችም እንዲሁ የድርጅቱ አባላት ሆነው ሌሎች ተማሪዎችን እንዲያጠምቁ እየተደረገ ነው፡፡ እንዲያውም አባል ያልሆነ ተማሪ በወደፊት ዕጣ ፈንታው እንደመፍረድ ተደርጎ እየታየ ነው፡፡

ኢህአዴግ ዜጎችን የማጥመቅ ሥራው በቀበሌ ስብሰባዎችም ያካሂደዋል፡፡ ቀበሌዎችም የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ማሰራጫ ማዕከላት ለማድረግ እየተሞከረ ነው፡፡ በተለይ መንግሥት በተፈጠረው የኑሮ ውድነትና ረሃብ የተነሳ በከተሞችም መልሶ የሸቀጥና የምግብ አቅራቢ እየሆነ ነው፡፡ ይህም እግረ መንገዱ የድጋፍ መሰባሰቢያ መድረክ እየደረገው ይገኛል፡፡ በቅርቡ የተቋቋሙት የትምህርትና የወረዳ ኔት የቴሌቪዥን ስርጭቶችም ዜጋን ለማጥመቅ በመሳሪያነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ይህ የኢህአዴግ አካሄድ ውጤቱ የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም ሙከራው ግን እያንዳንዱን ዜጋ በማጥመቅ ለመቆጣጠር ነው፡፡

ኢህአዴግ እያንዳንዲን ዜጋ ለመቆጣጠር እየጣረ ያለው የሚያራምደውን ርእዮተ ዓለም በማስረጽ ብቻ አይደለም፤ በድርጅታዊና አስተዳደራዊ መንገድም ሊቆጣጠረው ይሞክራል:: በአሁኑ ጊዜ ኢህአዴግ በተቻለ መጠን እያንዳንዱን ሰው የድርጅት አባል ሊያደርገው እያሞከረ ነው:: ራሱ በሰጠው መግለጫ እንኳ ከ4 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የድርጅቱ አባል ሆኗል:: ይህም በአባልነት ተቆጣጥሮ ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚያደርገው ሙከራ ነው:: በቀጥታ በድርጅቱ ያልታቀፉን ወገኖችም የተለያዩ ኢህአዴግ ደጋፊ በሆኑ ማኅበራት እንዲደራጅ ይደረጋል:: በሴቶች፣ በወጣቶች በአርሶ አደሮች አሁን ደግሞ በወጣቱ ሊግና በሴቶች ሊግ በማደራጀት ብዙ ሚልዮን ዜጎችን ለማሰባሰብ እየጣረ ይገኛል:: በነዚህ ድርጅቶች ያልታቀፈ ዜጋ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ስለሚቸገር ደግሞ ወደደም ጠላም በአባልነት እንዲታቀፉ ይደረጋል::

ኢህአዴግ በድርጅትና በማኅበር ሊያሰባስባቸው ያልቻሉትን በቁጥጥሩ የሚያስገባበት ስልትም ዘይዷል:: በገጠርና በከተማ መንግሥታዊ አካላትና የኮሚኒቴ ፖሊስ የሚባሉ አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል:: እያንዳንዱ ዕድሜው ለዓቅመ አዳም የደረሰ ዜጋ በመንግሥታዊ ቡድኖች መካተት እንደ ግዴታ ይታያል:: የኮሚኒቴ ፖሊስ አደረጃጀትም የውዴታ ግዴታ ዓይነት ነው:: እነዚህ አደረጃጀቶች ሲጠቃለሉ እያንዳንዱ ዜጋ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ቁጥጥርና ተጽእኖ ስር ይሆል ተብሎም ይገመታል:: ይህ አካሄድ እጅግ ፀረ ዴሞክራሲና አምባገነን የሚባሉ ፓርቲዎችና መንግስታት የሚከተሉት ነው:: ኢህአዴግ እየተከተለ ያለውም ይህንኑ ነው::

### 4.1.7 ***የሕግ የበላይነትን የሚጻረር አቅጣጫ***

የሕግ የበላይነት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የፍትሕ አካላት ነጻነት፣ ተጠ ያቂነትና ግልጽነት ሊሰፍኑ ይገባል:: ሆኖም የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚከተለው አቅጣጫ ይህን የሚጻረር ነው:: የፍትሕ አካላት በኢህአዴግ ተጽእኖ ሥር መሆቸውና ነጻነት እንደተነፈጋቸው ቀደም ብሎ ተገልጿል:: ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም:: ዳኞችና ሌሎች የፍትሕ ሠራተኞች ባለሥልጣናቱ ሲያጠፉ ደፍረው ሊከሷቸውና ተጠያቂ ሊያደርጓቸው አይችሉም:: እንዲያውም ህቅን ተከትለው ለመወሰን የሚሞክሩት አደጋ ላይ ይወድቃሉ:: ሥራቸውን ያጣሉ የደረጃ ዕድገት ይነፈጋሉ:: እስከ አሁን ድረስ በፖለቲካ ምክንያትና እጅግ ግልፅ ሆኖ ሊደበቅ ያልቻለ ወንጀል ካልሆነ በስተቀር ሕግን ተላልፎና

ጥፋት ፈጽሞ ከሥልጣን የተነሣ ከፍተኛ ባለሥልጣን አልታየም ። ብዙ ጊዜ የጥቃት ሰለባ የሚሆኑት ዝቅተኛ ሹማምንት ብቻ ናቸው። ይኸም ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፖለቲካ የሕግ የበላይነትን የሚጻረር መሆኑን ያመለክታል።

በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አካሄድ ተጠያቂነትና ግልጽነትም ተጓድሏል። በመሠረቱ ዴሞክራሲ ባልሰፈነበት ሁኔታ ግልጽነትና ተጠያቂነት መጓደሉ አይቀሬ ነው። ግልጽነትና ተጠያቂነት ለመጓደሉ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ የኢህአዴግ ፓርቲ አባላት ራሳቸውም የሚገነዘቡት ነው። ብዙ ጊዜ ችግር ተፈጥሯል ተብሎ በገፍ የሚወገደው የታችኛው የፓርቲ አባል እንጂ የላይኛው አባል አይደለም። የላይኛው ፓርቲ አመራር ሊወገድና ሊወቀስ ቀርቶ ሊጠየቅም አይችልም። በዚህ ጉዳይ ሕዝብ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ቢያቀርብም ሰሚ አያገኝም። ለዘመናት የሥልጣን እርካቡን ተቆናጥጠው ያሉት የኢህአዴግ የአመራር አባላት የሚያስጠይቅ ጥፋት ስለሌላቸው አይደሉም። የግል ጉዳይ ቀርቶ በአገር ጉዳይ የሚያስጠይቁ በርካታ ጥፋቶችም ተፈጽመዋል። ዝግጅት ያልተደረገበት የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት፣ የብዙ ዜጎችን ህይወት የቀጠፉ ግጭቶች፣ መጠን ያለፈባቸው በሰላማዊ ዜጎች የደረሱ ጥቃቶች፣ ወዘተ. በርካታ ጥያቄዎችን እያስነሱ ቆይተዋል። ሆኖም የፓርቲው አመራር ካለው ያልተገደበ ሥልጣን የተነሳ ተጠያቂ ሊሆን አልቻለም። በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሕግ የበላይነት አልሰፈነም የሚባለውም ለዚሁ ነው።

### 4.1.8 <u>የብሄር ብሄረሰቦች የይስሙላ መብት</u>

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሁሉም በላይ ለመደቦችና ለቡድኖች መብትና ጥቅም እንደቆመ ይገልጻል። ከዚህ የተነሣም በአገራችን የብሄር ብሄረሰብ መብቶች ጠበቃና የበላይ ጠባቂ ሆኖ ለመታየት ይሞክራል። ይህን በማስረጃነት ለማስደገፍም የአገራችን ብሄር ብሄረሰብ ጽንፈኛ መብት ሕገ መንግስታዊ እውቅና ያገኘው በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፕሮግራም አማካይነት መሆኑን በኩራት ይገልጻል። በእርግጥ የአገራችን የብሄር ብሄረሰብ መብት የራሳቸው የብሄር ብሄረሰቦች ትግል ውጤት ነው። መብትና ጥቅም በማንኛውም ፓርቲ የሚቸር አይደለም። የአንድ ፓርቲ ችሮታ ከሆነም ዘለቄታ አይኖረውም። ሆኖም ኢህአዴግ ግዙፍ የሆነውን የብሄር ብሄረሰቦች የመገንጠል መብት አስከብሪያለሁ ቢልም እውነታው ከዚህ የተለየ ነው። እስከ አሁን ድረስ የመገንጠል ጥያቄ አቅርቦ ተግባራዊ ያደረገ ብሄር ወይም ብሄረሰብ የለም። መገንጠል ቀርቶ በክልል ለመዋቅር ያቀረቡትን እንደነ ሲዳማ ያሉ ብሄሮች ጥያቄም ተቀባይነት

አላገኘም:: ይህ ከፍተኛ ጥያቄ ቀርቶ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ራሳቸውን የማስተዳደር መብትም አልተሰጣቸውም:: የብሄር ብሄረሰቦች አስተዳደር ስልጣን ጨብጦ ያለው ኢህአዴግ ራሱ ነው:: ሌላው ቀርቶ በየክልሉ «በህዝቡ ምርጫ» ለስልጣን የበቁትን አስተዳዳሪዎች እንኳ ሲፈልግ የሚሾማቸው ሲፈልግ የሚሽራቸው ናቸው:: ከዚህ ሌላ አብዛኛዎቹ የክልሎች ምክር በት አባላት የኢህአዴግ አባላት ስለሆኑ በኢህአዴግ ቀጭን ትእዛዝ የሚመሩ ናቸው:: ኢህአዴግ ከአንድ ማዕከል የሚያዛቸው ናቸው:: በመሆኑም የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተፈጻሚነት የይስሙላ ሆኖ ቀርቷል::

በእርግጥ በኢህአዴግ ሥልጣንና ፖለቲካዊ አቅጣጫ ከባድ ተጽእኖ በማያስከትሉት ጉዳዮች ላይ ክልሎች የተሻለ መብት አላቸው:: ክልሎች ቋንቋቸውና ባህላቸውን ለማዳበር መቻላቸው የዚህ ውጤት ነው:: ከዚህ ውጭ ያሉት ፖለቲካዊ ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ግን በጠንካራ ማዕከላዊነት የተተበተቡ ናቸው:: ይህ የኢህአዴግ በክልሎች የሚያደርገው ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት እንደሌላው ሁሉ የብሄር ብሄረሰቦችን መብትና ፌደራሊዝምን የይስሙላ አድርጎታል:: የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተማከለ ስልጣን የማጠናከር አባዜና የብሄር ብሄረሰቦች መብት እጅግ ተጻራሪ ሆነዋል:: የእያንዳንዱ ክልል አመራር በማእከላዊው የኢህአዴግ ሥልጣን ይሁንታ መቀጠሉ ደግሞ በመጠቃቀምና በጌታና ሎሌ ግንኙነት የተመሠረተ እንጂ የብሄር ብሄረሰብ መብት በሚፈቅደው መርህና በሕገ መንግሥቱ ላይ ተመሥርቶ እንዳልሆነ መመልከቱ ይቻላል::

## 4.2 <u>የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በኢኮኖሚው ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች</u>

### 4.2.1 <u>የልማታዊ መንግሥት ችግር</u>

ኢህአዴግ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ መለያ በማድረግ ልማታዊ መንግሥት የሚል አቅጣጫ እንደሚከተል ገልጿል:: ይህ በሊቀመንበሩ የቀረበውና አሁን የድርጅቱ መመሪያ እንዲሆን የተደረገው የኢኮኖሚ አቅጣጫ የመንግሥት ሚና በኢኮኖሚው በማጉላት ቁጥጥሩን የሚያጠናክርበት ዘዴ ነው:: በአንድ በኩል ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ውለታ መሠረት የሊቨራል ኢኮኖሚ አራምዳለሁ ሲል በሌላ በኩል ደግሞ ከባህርይው የመነጨ ሁሉን ነገር ለመቆጣጠር ካለው ፍላጎት የተነሳ መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ ያለውን ቁጥጥር ከፍ የሚያደርግ አቅጣጫ ሊከተል ይፈልጋል::

በእርግጥ ከሊቨራል የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ተነስቶም ቢሆን የመንግሥት ሚና በኢኮኖሚው መኖር የለበትም ሊባል አይገባም:: እንዲያውም የገበያ ሥርዓቱ ገና

ባልዳበረበት ባልበለፀጉት አገሮች መንግሥት በኢኮኖሚው የሚኖረው ሚና ከፍ እንዲል ያደርገዋል። ይህ ማለት ግን የፖለቲካ ሥልጣን ለማጠናከር ተብሎ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ጣልቃ በመግባት ኢኮኖሚውን መቆጣጠር አለበት ማለት አይደለም። ኢህአዴግ እያደረገ ያለው ግን ይህንኑ ነው። ኢህአዴግ የፋይናንስ ተቋማትን፣ የፓርቲ የንግድ ድርጅቶችንና መሬትን በመቆጣጠር ኅብረተሰቡን በቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት ይፈልጋል። ልማታዊ መንግስት በሚል ጽሑፉ ባስቀመጠው አመለካከት ደግሞ የተወሰነውን ባለሀብት ኪራይ ሰብሳቢና ጥገኛ ብሎ በመፈረጅ የራሱ ደጋፊዎችን ብቻ ለማጠናከርና ለመፍጠር ይጥራል። ኢህአዴግ ኪራይ ሰብሳቢ ወይም ጥገኛ የሚላቸው ራሱ ባስቀመጠው ቀመር እንጂ የኢኮኖሚው ሕግጋት በፈጠረው ክስተት ላይ ተመስርቶ አይደለም። ለኢህአዴግ ታማኝና አደግዳጊ ያልሆኑ ባለሀብቶች በጥገኝነትና ኪራይ ሰብሳቢነት ተፈርጀው ከእንቅስቃሴያቸው ሊስተጓጐሉ ይችላሉ። ይህም ኢኮኖሚውን ሊጐዳ የሚችል አካሄድ ነው።

በኢህአዴግ የልማታዊ መንግስት ፅንሰ ሐሳብ መሠረት ዋነኛው የልማት ኃይል ተደርጎ እየተወሰደ ያለው የገጠሩ ሀብታም ገበሬ ነው። ኢህአዴግ ከሚያቀነቅናቸው የኢኮኖሚ ፅንሰ ሐሳቦች መካከል እጅግ አደገኛ ሊሆን የሚችለውም ይህ ሊሆን ይችላል። በካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሕግጋት ዘመናዊው የኢኮኖሚ ዘርፍ ክምችት የሚኘው በከተሞች ነው። ከተሞች የቴክኖሎጂ፣ የእውቀትና የክህሎት ማዕከላት ናቸው። ጥንትም ቢሆን የካፒታሊስቱ ሥርዓት አቆጥቁጦ ያደገው በነዚህ ማእከላት ነው። የሀብት ፍሰትም ከገጠር/ግብርና/ ወደ ከተማ ነው። ይህን የሀብት ክምችት ተጠቅመው የአገርን ኢኮኖሚ የገጠሩን ጭምር ሊለውጡ የሚችሉ ወገኖች የሚገኙትም በከተማ ነው። ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ኢህአዴግ በከተማው ኗሪ ተቀባይነት ስላጣ አዲስ ኢኮኖሚውን ለመምራት የሚችል መደብ ገጠር ውስጥ እፈጥራለሁ በማለት ቁርጠኝነቱን ገልጿል። የኢኮኖሚ ሕጉ ጠልፎ ስለሚጥለው ሊሆንለት ባይችልም አካሄዱ ግን አደገኛ ነው፡ ኢህአዴግ የራሱ የሆነ የሀብታም ገበሬ መደብ ለመፍጠር ቆርጦ ከቀጠበለበት የአገሪቱ ፖሊሲዎች ሁሉ ይህን ለማሳካት መመቻቸታቸው የማይቀር ይሆናል። ይህም ከተሞች ዳብረው የኢኮኖሚ መሪነታቸው እንዳያረጋግጡና ዕድገቱን በዘላቂነት እንዳያስቀጥሉ እንቅፋት ከመሆን አያልፍም።

በኢህአዴግ የልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ መሠረት አጋራዊ ከበርቴው በጥርጣሬ የሚታይ ነው። እንዲያው ኢህአዴግ አገራዊ ከበርቴውን ወላዋይ በሚል ፈርጆታል። ሆኖም በካፒታሊስት ስልተ ምርት አገራዊ ከበርቴው ወሳኝ ሚና የሚጫወት መደብ ነው። ይህን መደብ አግልሎ ዝቅተኛ ካፒታል፣ እውቀትና ባህል

ያለውን ሀብታም ገበሬ መሠረት በማድረግ ዘላቂ ዕድገትና ልማት አረጋግጣለሁ ማለት ጭራሽ የማይሆን ነው። የሚያሳዝነው ነገር ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል የአገራችን ኢኮኖሚ በቤተ ሙከራነት መጠቀሙን ነው። ስለሆነም የልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሐሳብና ፖሊሲ ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠርና የራስን ደጋፊ ኃይል ለመፍጠር ከማለም ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

4.2.2 <u>ኢኮኖሚን በፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀም</u>

በአገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መንግሥት የሚኖረው ሚና በተመለከተ በርካታ ክርክሮች ሊነሱ ይችላሉ። መንግሥት ፈጽሞ በኢኮኖሚው እጁ ማስገባት የለበትም ከሚል ጀምሮ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት ሊኖረው ይገባል እስከሚል ክርክሮች ሊነሱ ይችላሉ። እነዚህ ክርክሮች መነሣታቸው አግባብነት ያለው ነው። ሆኖም የኢሀአዴግ አካሄድ ከዚህ ለየት ያለ ነው። ኢሀአዴግ በመሠረቱ ኢኮኖሚው ሥልጣን ለማራዘምና ለማደላደል እየተጠቀመበት ይገኛል። በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠራቸው የአገር ሀብቶች ለፖለቲካ ፍጆታና ሥልጣኑን ለማጠናከር እየተጠቀመባቸው እንደሚገኝ በርካታ አብነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢሀአዴግ ወሳኝ የፋይናንስ ተቋማትን ስለተቆጣጠረ የሚፈልጋቸውን ወገኖች ብድር በመለገስ ለማጠናከር የማይፈልጋቸውን ደግሞ ለማዳከም ይገለገልበታል። በአገራችን አሁን ከፍተኛ ሀብት አከማችተዋል የሚባለት ወገኖች አንዱ ምንጫቸው ይህ ፖሊሲ መሆኑ ይታወቃል። ልማታዊ ባለሀብቶች ተብለው የሚታወቁት የአገሪቱን የፋይናንስ አቅም በከፍተኛ ደረጃ ተጠ ቃሚዎች ሲሆኑ ጥገኞች የተባሉት ግን ዕድገታቸው እንዲዳከም ይደረጋል። ስለሆነም መንግሥት የተቆጣጠራቸው የፋይናንስ ተቋማታት የአድልዎና የሙስና ማእከላት ከመሆናቸው ባሻገር መንግሥት በመሣሪያነት የሚገለገልባቸው ሆነዋል።

መሬትም ሌላው ለፖለቲካዊ መሣሪያነት የዋለ የአገር ሀብት ሆኗል። በገጠር መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ነው ቢባልም በተጨባጭ ግን የመንግሥት ባለሥጣናት ሀብት ሆኗል። ሕጋዊ ባልሆነ ወይም ሕግን ተገን በማድረግ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ባለሥልጣናት የመንግሥት መሬት እንደዘረፉ አገርና መንግሥት ያወቀው ነው። በገጠ ር ያሉ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው እንዳይፈናቀሉ ሲሉ የካድሬዎች አገልጋይ ሊሆኑ እንደሚገደዱም ራሳቸው በስፋት የሚናገሩት ነው። ገበሬው ነጻነቱ ተነጥቆ በካድሬዎች ተጽእኖ ሥር የወደቀው መንግሥት ወሳኝ የሆነውን ሀብት ተቆጣጥሮ ዋስትና ስለከለከለው ነው። የመሬት ጉዳይ ከተነሳ ዘንዳ በአሁኑ ጊዜ የአርሶ አደሮች ከባድ

ችግር የሆነው ከመሬታቸው በአስገዳጅ መፈናቀላቸው -ጽሽፀቸተጽደ መሆናቸው? ነው:: ለአበባ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለፋብሪካ፣ ወዘተ. እየተባለ ያለ በቂ ካሳና ዘላቂ ዋስትና የሚፈናቀለው ገበሬ ቁጥሩ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ነው:: አቤት ብሎ ሰሚ ስላጣም እያለቀሰና እያዘነ የሚኖረው ገበሬ ቁጥር ስፍር የለውም:: ይህ በከተሞች አካባቢ የተጀመረው ክስተት አሁን ራቅ ወደአሉ መንደሮችም እየገባ ነው:: የኢህአዴግ ልማታዊ መንግሥት አንዱ ውጤት ይኸው ነው::

መንግስት መሬትንና የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠር እያሳደረ ያለው ጫና እንዳለ ሆኖ በእርዳታ የሚገኘውንና ለሕዝብ የሚከፋፈለውን ገንዘብ ሳይቀር በፖለቲካ መሣሪያነት እየተጠቀመበት ነው: በገጠር በሴፍቲኔት መርሃ ግብር ለመታቀፍ በከተማም ብድርና እርዳታ ለማግኘት ቢያንስ በኢህአዴግ ቁጥጥር ባሉት ማኅበራት መሳተፍ የግድ ይላል:: ከዚያ ያለፈም በአባልነት መመዝገብ አስፈላጊ ይሆናል: ይህ አካሄድ በአገሪቱ በሙሉ የሚሠራበት ነው:: በመሆኑም ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው ዕርዳታን በመሣሪያነት ተጠቅሞ ደጋፊና አባል የማሰባሰብ ተግባር አደገኛ እየሆነ ነው::

መንግሥት በአገራችን ከፍተኛው ቀጣሪ ነው:: በመንግሥት ደመወዝ የሚተዳደሩ ወገኖች እጅግ በርካታ ናቸው:: በቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብም ለደመወዝና ለውሎ አበል ይውላል:: ይህን በቢልዮኖች የሚቆጠር የመንግሥት ገንዘብ በማስማራት ሠራተኛ ቀጣሪ በመሆኑ ኢህአዴግ አባላትን ለመመልመልና ለማጠናከር እየተጠ ቀመበት ይገኛል:: የመንግሥት ሠራተኛ የኢህአዴግ አባል እንዲሆን ከመወትወቱ በተጨማሪ አባል ካልሆነ እንደጠላት እየተቆጠረ ከዕድገት ከሥልጠናና ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲቀር ይደረጋል:: ይህን የኢህአዴግ አካሄድ የማይቀበሉ ሥራውን እየለቀቁ ሲሄዱ አብዛኞዎቹ ደግሞ አማራጭ በማጣት ለኢህአዴግ አሠራር ተገዢ ሆነው ይገኛሉ:: እነዚህ የአገሪቱን ልማትና ዕድገት እንዲመሩ የዜጎች አደራ የተጣለባቸው ሠራተኞች በአንድ ፓርቲ አስተሳሰብ ተቀፍድደው እንዲኖሩ መደረጋቸው በልማትና በዕድገት የሚያስከትለው ተጽእኖ ቀላል አይሆንም፤ የሠራተኛው ተነሳሽነትና ቁርጠ ኛነትን በመግደል እምቅ አቅምን ያጠፋል::

ኢህአዴግ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ደጋፊዎቹና አባላቱ ያልሆኑትን ለመመንጠር ቆርጦ የተነሣ ይመስላል:: መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /Buisness Processing Reenginering/ በሚል የጀመረው እንቅስቀሴ ሠራተኞች ለገዥው ፓርቲ ያላቸው ታማኝነት እንጂ ምያዊ ብቃታቸው ዋጋ የጣበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ከዚህ የተነሣም ብቃታቸው አንሶ ታማኝነታቸው የላቀ ሠራተኞች ከፍተኛ የምደባ ቦታ ሲያገኙ

በሙያቸው የበለጡትና ነጻ የሆኑት ግን ቦታ እንዲያጡ እየተደረገ ነው። በርካታዎቹም ከሥራ የመሰናበትና የመንሳፈፍ ሰለባ እየሆኑ ነው።

### 4.2.3 <u>ፍትሐዊነት የጐደለው የኢኮኖሚ አቅጣጫ</u>

ኢህአዴግ ቀደም ሲል በአጠቃላይ ለገበሬው የቆመ ድርጅት መሆኑን ይገልጽ ነበር። አሁን ግን ገበሬውን በሁለት ከፍሎታል። አንዱ ክፍል ሀብታም ገበሬ ሲሆን ሁለተኛውን ደግሞ ተስፋ የሌለው ወይንም መናጢ ገበሬ ብሎታል። ኢህአዴግ ቆርጦ የተነሣው ሀብታም ገበሬውን አጠናክሮ የሥልጣን መሠረቱ ለማድረግ ስለሆነ ተስፋ የሌለው ያለውን ገበሬ እንዲረሳ አድርጎታል። የዚህ ዓይነት ገበሬ እጣ ፈንታ ተቀጣሪ ሆኖ ማገልገል ነው ቢልም የገጠሩ ልማት ደካማ በሆነበት ሁኔታ በደህና ዋጋ ቀጣሪ ሊያገኝ አይችልም። በመሆኑም ወደ ከተማ በመፍለስ ሥራ ይፈልጋል። በኢህአዴግ ፖሊሲ ለከተሞች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ደግሞ እነዚህን የፈለሱ ሥራ አጥ ገበሬዎች ሊያስተናግድ አይችልም። በመሆኑም በገጠር ፍልሰትን ሲያስከትል በከተማ ደግሞ የሥራ አጦችን ክምችት ከፍ በማድረግ እጅግ የተቸገሩና ጎስቋላ ወገኖችን ያበራክታል።

ኢህአዴግ በከተሞች ትላልቅ ኢንዲስትሪዎች ተቋቁመው በርካታ ሥራ አጦችን እንዲቀጥሩ በማድረግ ፈንታ በአነስተኛ የሀብታም ገበሬዎች ኢኮኖሚ የተመሠረተ ኢኮኖሚ እገነባለሁ በማለቱና በከተማም ከመሠረታዊ ኢንዱስትሪዎች ይልቅ «ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች» ይበልጥ ትኩረት እሰጣለሁ በማለቱ የሚፈለገውን ግዙፍና አስተማማኝ ዕድገት ሊያስመዘግብ አልቻለም። ከዚህ በተጨማሪም ፍትሐዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ትኩረት ሰጥቶ አልተንቀሳቀሰም።

ኢህአዴግ ይህ የፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ጥያቄ ሲነሳ የሚከተለው የኢኮኖሚ አቅጣጫ በባህርይው ፍትሕን ስለሚያረጋግጥ ችግር እንደማይኖረው ይገልጻል። ሆኖም ሀብታም ገበሬውን የሚሸልምና አቅም የሌለውን ደሀ ገበሬ የሚያንቋሽሽና የሚገድል ፖሊሲ በማንኛውም መስፈርት ፍትሐዊ ሊሆን አይችልም። ኢኮኖሚው የሚመራበት አቅጣጫ ካፒታሊስት ቢሆንም በዚህ ማዕቀፍ ሥር ሆኖ ሊደረግ የሚችለውን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ግን መጤን ይኖርበታል። አለበለዚያ የኢኮኖሚው አቅጣጫ ባህርይ ራሱ ፍትሕን ያስከትላል ማለት ከፍተኛ ስሕተት ይሆናል።

## 5. <u>የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲና አደጋው</u>

ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ የአገራችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ምንጭ መሆኑ ከፍ ብሎ ተገልጿል። ይህ ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው አቅጣጫ እንዲቆም ካልተደረገ ችግር ከመፍጠር አልፎ በአገሪቱ ሠላምና መረጋጋት አደጋን ሊያስከትል ይችላል። ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው ፖለቲካዊ አቅጣጫ የአምባገነንነትና የበላይነት አቅጣጫ ነው:: ኢህአዴግ በአገሪቱ ፖለቲካ የበላይነት ማረጋገጥ እንዳለበት ሳያወላውል ግልጽ አድርጎታል። ግልጽ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ተቃዋሚዎችን በማዋከብ፣ ዜጎችን በማሸበር፣ የፖለቲካ ምሕኅዳሩን በማጥበብ ብቸኛ ገዢ ፓርቲ ሆኖ ለመቀጠል እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። እንደውም ከአሁን ወድያ ለ30 እና ከዚያ በላይ ዓመታት በሥልጣን ለመቆየት እንደሚፈልግ የጃፓንና የስዊድን ፓርቲዎችን እያጣቀሰ ይገኛል። ይህ አካሄድ ሕገ መንግስቱን የሚጻረር ነው:: ሕገ መንግስቱ መድብለ ፓርቲና መድብለ ሐሳብ ተቀባይነት አግኝተው ዜጎች ፍትሐዊና ነጻ በሆነ መንገድ ተወዳድረው ሥልጣን ለመያዝ እንደሚችሉ ይደነግጋል። የኢህአዴግ አካሄድ ግን የዚህ ተጻራሪ እየሆነ ነው::

በአንድ አገር ውስጥ ሕገ መንግስት ተከብሮ ሥራ ላይ ካልዋለ ያለው አማራጭ የኃይልና የጡንቻ አገዛዝ ነው። እንደኛ ባለው እጅግ በተወሳሰበ ፖለቲካ የተጠመደ አገር ደግሞ እንኳን በአምባገነናዊ መንገድ በዴሞክራሲያዊ መንገድም ማስተዳደር አስቸጋሪ ይሆናል። የአገራችን ተጨባጭ እውነታ ውስብስብ የሆነው ፖለቲካ እጅግ ዴሞክራሲያዊና ስምምነት -ቸጸነሰጽነሰጭሰ? በሰፈነበት አግባብ ብቻ መረጋጋት፣ ልማትና አንድነት መፍጠር ይቻላል። አለበለዚያ የዜጎችና ብሄር ብሄረሰቦች መብቶች በተረገጠበት ሁኔታ አለመግባባት፣ ግጭት፣ በመጨረሻም መበታተንን ሊያስከትል ይችላል። ይህ አማራጭ የማይፈለግ ቢሆንም ገዢው ፓርቲ እየገፋ ያለው ግን ወደዚህ ወደ ማይፈለገው አቅጣጫ ነው::

ዛሬ በአገራችን የተለያዩ ተቃውሞዎችን በሰላማዊ መንገድ በማሰማት የሚገኙ ፓርቲዎች ይገኛሉ። ከዚህ ሌላም ትጥቅ አንግበው የሚዋጉ ወገኖች አሉ። እነዚህን ወገኖች በጡንቻና በኃይል ለመቆጣጠር መሞከር የሚያስከትለው አደጋ ቀላል አይሆንም። የሰው ህይወት ከማለፍና የአገር ሀብት ከመባከኑ በተጨማሪ እየቆየ ሲሄድ እንደሌሎች አገሮች መንግሥር አልባነትን አስከትሎ መበታተንና መለያየትንም ሊያስከትል ይችላል። ኢህአዴግ እየተከተለ ያለው አቅጣጫ መቋጫ ካልተበጀለት የተዳፈነ ቢመስልም ሊፈነዳ የሚችል ነው። የታመቀው ብሶት ሲፈነዳ ደግሞ ማስቆሙ ቀላል አይሆንም። ስለሆነም አደጋው ከወዲሁ መጤን ይኖርበታል።

6. <u>*አማራጭ መፍትሔው ምንድን ነው?*</u>

*ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚል እያራመደው ያለው አምባገነንነትን የሚያስከትል የፖለቲካ አቅጣጫ ካለው ሥልጣንን በብቸኝነት የመቆጣጠር ፍላጎት የሚመነጭ ስለሆነ አካሄዱ የሚበጅህ አይደለም፣ መንገድህን ለውጥ፣ ብሎ ማስለወጥ አይቻልም። እንዲያውም በዚህ አቅጣጫ እየተጓዘ ችግር ውስጥ በሚዘፈቅበት ጊዜ ይበልጥ አምባገነን ይበልጥ አፋኝ እየሆነ ከማይወጣበት ማጥ ውስጥ ይገባል። ይህ አደገኛ አቅጣጫውን ማስቆም የሚቻለው አደጋውን የተመለከቱ ዜጎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ቢያንስ ይህን አደጋ በመቀልበስ ዙሪያ ተሰባስበውና ተስማምተው አደጋውን ለማስቆም መሞከር ነው። ይህን ያደርጉ ዘንድም*

1ኛ/ ***በተቃዋሚዎች መካከል ያለውን አለመግባባት ማስወገድ፣***

*ተቃዋሚዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ከማጉላት ይልቅ በሚያስማሟቸው በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ ተገናኝተው አብረው በመሥራት በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ያላቸውን ተጽእኖ እንዲያድግ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህን ካደረጉ የአፈና መዋቅሮችን፣ የኢኮኖሚ ተቋማትንና በርካታ አባላትን በማቀፉ የማይበገር የሚመስለውን ኢህአዴግ ባላቸው የፖለቲካና የሞራል የበላይነት ሊያሸንፉትና ለአገራችን የሚበጅ አማራጭ ሊያስገኙ ይችላሉ። ስለሆነም ያላቸውን እምቅ አቅም አሳንሰው ሳያዩ በጋራ በመሥራት ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።*

*ተቃዋሚዎች ተበታትነውና በተናጠል ፋይዳ ያለው ሥራ ሊሠሩ አይችሉም። ፋይዳ ያለው ሥራ መሥራት ቀርቶ በወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለመደራደርና ለመወያየት የሚችሉ አይሆኑም። በእርግጥ አማራጭ ሆኖ ለማቸነፍ ብቻ ሳይሆን ለመደራደርም የኃይል ሚዛኑን መለወጥ አስፈላጊ ነው። አሁን ያሉት ከዘጠና በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች ባሉበት ሁኔታ ከቀጠሉ ለኢህአዴግ አገዛዛ እጅግ የተመቹ ይሆናሉ። ይኽ ሲባልም ለመቃወም ብቻ ተብሎ መሰባሰብ ይኖርባቸዋል ለማለት አይደለም። ቢያንስ ሊያቀራርባቸው የሚችሉ የተወሰኑ የጋራ ፖለቲካዊ ዓላማዎች ሊኖሯቸው ይገባል። ከፍ በለው የተጠቀሱት የአገራችን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት መቆም በራሱ መግባባትና ኅብረት ለመፍጠር በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም ለአገር ዕድገትና ለውጥ ሲሉ በመካከላቸው ሊኖሩ የሚችሉን መለስተኛ ልዩነቶች ወደ ጎን በመተው አንገብጋቢ በሆኑት አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመደራደርና በመወያየት ተባብረው ለመሥራት ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል።*

2ኛ/ *ገዥው ፓርቲ ሕገ መንግሥቱን እንዲያከብር መታገል፣*

በኢትዮጵያ የተጻፈ ሕገ መንግሥት አለ። በዚህ ሕገ መንግሥት በርካታ መሰረታዊ መብቶች ተደንግገዋል። ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በሕገ መንግስቱ ተደንግገዋል። የተቃዋሚዎች አማራጭ ከዚህ ሕገ መንግሥት ሊቀዳ ይችላል። ኢህአዴግ በአንድ በኩል ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን እንደሚያከብር እየገለጸ በሚያሰራጫቸው ሌሎች ሠነዶቹ ግና ሕገ መንግሥቱን የሚጻረሩ ብቻ ሳይሆኑ ሕገ መንግሥቱን ከሥሩ የሚንዱ አቋሞችን በማራመድ ላይ ይገኛል። የልማታዊ መንግሥት ፅንሰ ሐሳብና የሥልጣን የበላይነት /ጠቅላይነት/ ፅንሰ ሐሳብ ሕገ መንግስቱን በመሰረቱ እንደሚጻረሩ ይዘታቸው የተመለከተ ሁሉ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል።

ኢህአዴግ ሕገ መንግሥቱን አክባሪና አስከባሪ በመምሰል ሌሎችን በሕገ መንግሥት አፍራሽነት ቢከሳቸውም ሕገ መንግስቱን እየቦረቦረና እያፈረሰ ያለው እሱ መሆኑን ተገንዝቦ ትግል ማፋፋም ያስፈልጋል። ኢህአዴግ ሕገ መንግሥቱን በሚገባ ካከበረ የጨዋታው ሜዳ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። ያኔ የፈለገውን የፖለቲካ አቅጣጫ ቢያራምድም አግባብነት ያለው ይሆናል። አሁን ግን በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩትን መለስተኛ ድንጋጌዎችን እንኳ እያከበረ አይደለም። አገሪቱን በምርኮ እንደተቆጣጠራት በመቁጠር ከሕገ መንግሥቱና ከሕግ በላይ በመሆን ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ይገኛል። የተቃዋሚዎች አንዱ ተግባርም ኢህአዴግ ሕገ መንግሥቱን እንዲያከብር ማድረግ ይሆናል።

3ኛ/ *የፖለቲካ ምኅዳሩ እንዲሰፋ መታገል፣*

በአገራችን በአሁኑ ጊዜ የፖለቲካ ምኅዳሩ እጅግ ጠቦ ይገኛል። ከጊዜ ወደ ጊዜም ምኅዳሩ ይበልጥ እየጠበበ እየሄደ ነው። ይህ ሁኔታ በአገሪቱ ሊያስከትለው የሚችለው አደጋ በቀላሉ መታየት የለበትም። ኢህአዴግ ምኅዳሩን እንዲያሰፋ ጠንካራ ጫና ሊደረግበት ይገባል። ጫናው መምጣት ያለበትም ከአገሪቱ ዜጎች ነው። ምክንያቱም የፖለቲካ ምኅዳሩ መጥበብ የሚጐዳው ፖለቲከኞችን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋን ነው። ሕዝቡ አሁን ያለውን አስቸጋሪ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲገነዘብ ማድረግ ተገቢ ነው። በተለይ ኢህአዴግ የአገሪቱን ፖለቲካዊ መልክዓ ምድር ብቻውን ለመቆጣጠር እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በማስቆም ረገድ ዜጎች የበኩላቸውን እንዲወጡ መጠየቅ አስፈላጊ ይሆናል።

የፖለቲካ ምኅዳሩ የማስፋት ጉዳይ የአገራችን ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የአካባቢያችንና የዓለም ዓቀፍ ኃይሎችም ጭምር ነው:: በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ምኅዳሩ ከጠበበ ለብጥብጥና ለሰላም እጦት ምክንያት ይሆናል:: ኢትዮጵያ ታክል ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላት አገር ከታመሰች ደግሞ የአካባቢው ሃገራት ይሁን የዓለም ዓቀፍ ኃይሎች ጥቅም ሊጐዳ እንደሚችል ማስገንዘቡ ተገቢ ይሆናል:: የኢትዮጵያ መረጋጋትና ሠላም በሠራዊትና በጡንቻ ብቻ ዋስትና ሊያገኝ እንደማይችል ግንዛቤ መውሰድ ይኖርበታል:: የመንግስቱ ኃይለማርያም፣ የአፄ ኃይለ ስላሴና የሰይድ ባሬ መንግሥታት በቂ ጡንቻ እንደነበራቸው የቅርብ ታሪካቸው ይመሰክራል:: ሆኖም በዚህ ጡንቻቸው ሰላምና መረጋጋትን ሊያረጋግጡ አልቻሉም:: የሰላምና መረጋጋት ዋነኛ መሠረት ዴሞክራሲና የፖለቲካ ኃይሎች ስምምነት ነው:: በመሆኑም በኢትዮጵያ ጥቅማቸውን ለማራመድ የሚፈልጉ ኃይሎችም ይህን ተገንዝበው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ማሳሰብ ያስፈልጋል:: ወሳኙ ጉዳይ የራሳችን እንቅስቃሴ ቢሆንም እነዚህ ኃይሎችም የተወሰነ ሚና ይኖራቸዋል:: በመሆኑም የፖለቲካ ምሕኅዳሩን ለማስፋት በሚደረገው ትግል የተቻላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል::

4ኛ/ ***ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲካሄድ ለማስቻል መንቀሳቀስ፣***

የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ዳግም የሚፈተንበት ጊዜ ተቃርቧል:: 2002 ዓ.ም የምርጫ ጊዜ ነው:: ይህ ምርጫ የአገራችንን የቅርብና የሩቅ እድል የሚወስን ይሆናል:: በተነጻጻሪ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ከተካሄደ የኢትዮጵያ መፃኢ እድል ብሩህ ይሆናል:: የ1997 ዓ.ም ዓይነቱና እሱን ተከትሎ የተካሄደው የአካባቢ ምርጫ ዓይነት ከሆነ ግን የኢትዮጵያ መፃኢ እድል ተስፋ ቢስ ይሆናል:: አሁን ያለው የኢህአዴግ አካሄድ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዳይካሄድ የሚያደናቅፍ እንደሆነ ከወዲሁ እየተያ ነው:: የመገናኛ ብዙሐን ነጻነት መገደቡ፣ የሲቭል ማኅበረሰብ እንቅስቃሴ በሥጋት ታይቶ ለመቆጣጠር መሞከሩ፣ ተቃዋሚዎችን በጠላትነት መፈረጁ፣ ተቃዋሚዎችን ከተቻለ በአጋርነት ለማሰለፍ አለበለዚያም ለመበተን እንቅስቀሴ መካሄዱ ሁኔታው ከወዲሁ ተስፋ ቢስ ያደርገዋል:: ሆኖም በነዚህ እንቅስቃሴዎች ተስፋ ባለመቁረጥ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሄድበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከወዲሁ መደራደር አስፈላጊ ይሆናል:: ድርድሩ ሕዝቡ አውቆት የመፍትሔው አካል የሚሆንበት ሁኔታም ማመቻቸት ያስፈልጋል::

5ኛ/ ***የጠራ አማራጭ የፖለቲካ ፕራግራም፣ ስልትና ስትራቴጂ ይዞ መውጣት፣***

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ችግሮችን ለመዳሰስ ተሞክሯል:: የተዳሰሱት ችግሮች እዛ እያለም መፍትሔዎች ናቸው:: ዋናዎቹ የተጠቀሱት የአብዮታዊ

ዴሞክራሲ ችግሮች አንስቶ በመነጋገር መፍትሔዎችን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ሆኖም መፍትሔዎቹ አነጋጋሪ ሊሆኑ ስለሚችሉ ጊዜ ሳይወስዱ በነዚህ ዙሪያ መነጋገርና የጋራ የፕሮግራም ረቂቅ መንደፍ ተገቢ ነው፡፡ በፕሮግራሙ ረቂቅ የሚቀርቡ ዓላማዎች ከታወቁ በኋላ ደግሞ ስልትና ስትራቴጂ ለመንደፍ ጥረት ማድረግ ያሻል፡፡ በዚህ ረገድ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ችግሮች አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ኢህአዴግ አምባገነናዊ ሥርዓት ለመገንባት ሲል የፖለቲካው የበላይነት የማረጋገጥ ንድፍ ሐሳብ ሰንዝሮ ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ተቃዋሚዎችም ይህን አደገኛ አካሄድ ሊያመክኑ የሚችሎ ስልቶችና ስትራቴጂ ነድፈው በጋራ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ሊያሳኩ ካልቻሉ እንቅስቀሴያቸው ከወዲሁ እንደተጨናገፈ ሊቆጥሩት ይገባል፡፡

## ዋቢ የተደረጉ ጽሑፎች


1. A.Rezinko 1978. The Comintern and the East: Strategy and Tactics. Progress Publishers, Moscow
2. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ኅዳር 1983
3. የኢትዮጵያ ላብ አደሮች ፓርቲ፣ ታህሳስ 1983፣ ወያናይ ናይ ኢትዮጵያ ሸቃላይ ፕሮግራም /ትግርኛ/
4. አህአዴግ፣ ጥር 1983፣ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮገራም
5. ኢህአዴግ የሽግግሩ ጊዜ የትግለ ሂዴትና ቀጣይ ተግባራት /ትግርኛ/
6. ኢህአዴግ፣ነሓሴ1989፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መለያ እምነቶቻችን
7. ኢህአዴግ፣ ጥቅምት 1999፣ ልማት ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ
8. ኢህአዴግ ፣ጥቅምት 1999፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስትራተጅ ታክቲኮችና የአመራር ጥያቄ
9. Meles Zenawi: African Development: Dead Ends and New Beginnings

10 ኢህአዴግ ሰኔ 2000ዓም አገራዊ ለውጦች ቀጣይ ፈተናዎችና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሔዎች